<<ማኅበረ ቅዱሳን>> እግዚአብሔር ያከበራቸው የነቢያት፣ የሐዋርያት፣ የጻድቃን፣ የሰማዕታት በአጠቃላይ የቅዱሳን ገድል፣ ትሩፋትና አማላጅነት የሚዘከርበት በመሆኑ ይህን ስያሜ አግኝቷል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በልማት ተቋማት አስተዳደር በመጽሔት ዝግጅት ክፍል የሚታተም ትምህርታዊ መጽሔት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓተ እምነትና ክርስቲያናዊ ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ

፳፱ኛ ዓመት ቁጥር ፪
ጥቅምት ፳፻፲፬ ዓ.ም.

# ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ዲያቆን አሻግሬ አምጤ
አድራሻ፡-የካ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 01/02 የቤት ቊጥር 521/522
ስልክ +251- 911361580

**ከፍተኛ ሪፖርተር**
ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን

**ጸሐፊና ሌይ አውት ዲዛይነር**
ገነት ታደሰ

**አሳታሚ**
በኢ/ኦ/ተ/ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን ልማት ተቋማት
አ.አ አራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ስልክ +251-118-124222
ፖ. ሣ. ቊ.80078
ኢ.ሜይል magazine@eotcmk.org
የማኅበረ ቅዱሳን ሕዝብ ግንኙነት
ስልክ +251-962171717
የልማት ተቋማት ሽያጭና ስርጭት መምሪያ
ስልክ 0111540484/0111246184/0944259014
የማስታወቂያ ዝግጅት ክፍል ስልክ
0111246184/0913296480

## ማውጫ

**መልእክት ዘማኅበረ ቅዱሳን**
"ለተቸገረ የሚረዳ ብፁዕ ነው"................................ ፪
**ዐውደ ስብከት**
አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ.........፬
**ትምህርተ ሃይማኖት**
ናሁ እግዚአብሔር ይነብር ዲበ ደመና ቀሊል ወይመጽእ ውስተ ግብፅ (ኢሳ.፲፱፥፩) ...................................፮
**ዐብይ ጉዳይ**
የምንሠራውከሪፖርት ባለፈ ሕይወትን ለመታደግ ይሁን............ ፲
**ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ**
ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዉ አኃው ኅቡረ (መዝ. ፻፴፪፥፩)..... ፲፬
**እናስተዋውቃችሁ**
በሐዋርያት ከተማ ያለች ቤተ ክርስቲያን..................... ፲፮
**የነገዋ ቤተ ክርስቲያን**
የበዓላት ድምቀት ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት ያላት አስተዋጽኦ.....፳
**ኪነ ጥበብ**
"የሰላምታ ደብዳቤ"......................................፳፪
**ጥያቄዎቻችሁ መልስ**
..................................................................፳፮

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!!

# ‹‹ለተቸገረ የሚረዳ ብፁዕ ነው››

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ለችግር የተጋለጡ ወገኖቻችንን የምትደግፈው ኃላፊነቷ በመሆኑ ነው፡፡ የሰውን ልጅ ሁሉ የምትረዳውም ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት ሳትለይ ሰው መሆናቸውን በማየት ብቻ ነው፡፡ መመሪያዋም "ለድኃና ለምስኪን የሚያስብ ብፁዕ ነው፤ እግዚአብሔር ከክፉ ቀን ያድነዋል፡፡ እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፤ ሕያውም ያደርገዋል፤ በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፣ በጠላቶቹ እጅ አሳልፎ አይሰጠውም" የሚለው አምላካዊ ቃል ነው (መዝ.፵፥፩-፪)፡፡ ይህ ቃል ለተቸገረ መርዳት በእግዚአብሔር እንድንጠበቅ ከማድረግ በተጨማሪ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ድርጊታችንን ዓይተው፣ ሥራችንን ከግምት ውስጥ አስገብተው እንዲያመሰግኑን ምክንያት ይሆናል፡፡ ወደ ሃይማኖት እንዲመጡም የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በመዋቅርም ሆነ ልጆቿ በተናጠል ለተቸገሩት መድረሳቸው ሁሉን ሰብሳቢና ለሁሉ ደራሽ ሲያሰኛት ኖሯል፡፡ ሐኪም ሰዎችን የሚያክመው ዘር ሳይለይ፣ ቋንቋ ሳይመርጥ ፣ ወገን ጠላት ብሎ ሳይከፋፍል በጦርነት ላይ ጉዳት የደረሰባቸውን ሁሉ መሆኑ ይታወቃል፡፡ የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ርዳታና ድጋፍ ደግሞ ከሐኪምም በላይ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተችበት ጊዜ አንሥቶ በየዘመናቱ ለተቸገሩት ስትደርስ የኖረችው አምላካዊ ትእዛዝ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጅ ሕይወት ለአደጋ መጋለጥ ስለሚያሳስባትም ጭምር ነው፡፡

ቤተ ክርስቲያን እንዲህ በማድረጓም "መልካሙን ሥራችሁን ዓይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያመሰግኑት ዘንድ እንዲሁ ብርሃናችሁ በሰው ፊት ይብራ" የሚለውን አምላካዊ ቃል በተግባር ትገልጣለች (ማቴ.፭፥፲፮)፡፡ ይህም አሕዛብ ሥራዋን አይተው የክርስቶስ አካል፣ የቤተ ክርስቲያን አባል እንዲሆኑ መንገድ ይከፍታል፡፡ በዘመናችን በተከሠተው ጦርነት ወገኖቻችን ሀብትና ንብረታቸውን አጥተዋል፡፡ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ባህል አካባቢ ሳይለይ ለስደትና ለረኃብ ተዳርገዋል፡፡ በጦርነት የተሰለፉትም ከግራም፣ ከቀኝም እየቆሰሉ ነው፡፡ ችግሩ ያሳሰባቸው ወገኖች የተፈናቀሉትን ለመርዳት አቅማቸው የፈቀደውን በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ምንም እንኳ ርዳታን ምክንያት አድርገው ለችግር በተጋለጡ ወገኖቻችን ቊስል እንጨት የሚሰዱና ሕመማቸውን የሚያባብሱ አካላት ቢኖሩም ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን የምትረዳው ሰው በመሆናቸው ብቻ በመሆኑ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን በማጣት ከችግራቸው እንዲላቀቁ፣ ከሥነ ልቡና ስብራት ተላቀው ነገ አዲስ ሕይወት መኖር እንዲጀምሩ ለማድረግ ጭምር ነው፡፡ የተጎዱት ወገኖቻችን ከዚህ ደረጃ እንዲደርሱ ብዙ መሥራት፣ ልጆቿን አስተባብራ ለተቸገሩት ሁሉ በመድረስ ከመከራ እንዲያወጧቸው ማድረግ ይኖርባታል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ዘር፣ ሳትመርጥ፣ ቋንቋ ሳትለይ ሁሉንም የምትረዳውም ተልእኮዋ ሰማያዊ በመሆኑ ነው። በተጎዱት አካባቢዎች የሚገኙ አባቶች ሆስፒታል ሔደው የቈሰሉ ወገኖቻችንን ሲጠይቁ የተመለከትነው፣ ከችግረኞች ጋር አብረው በዓል ሲያከብሩ ያየነው ሰዎች ችግር በገጠማቸው ጊዜ እንድትደርስላቸው ከአምላኳ በመታዘዟ ነው።

በግል ከመሮጥ ይልቅ እየተሰባሰቡና እየተደራጁ ለችግረኞች የሚያስፈልጋቸውን በማሰባሰብ ማድረስ ያስፈልጋል። ክርስቲያኖች ይህን የምናደርገው የሰው ልጅ ሁሉ ጉዳት ጉዳታችን መሆኑን ስለምናምንና በሌሎች የደረሰ ክፉ ነገር እንዲደርስብን ስለማንፈልግ ነው። ምእመናን ልጆቿ ለችግር ለተጋለጡት የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብና የቍሳቁስ ድጋፍ ለማሟላት የበኩላችንን እናበርክት የምንለው እንደሌሎች በችግረኞች ጉዳት ለመነገድ እና ታዋቂነትን ለማግኘት ሳይሆን ለተቸገረው ሁሉ መድረስ ከአምላካችን የታዘዝነው በመሆኑና እየተሠራ ካለው የበለጠ መሥራት ስለሚጠበቅብን ጭምር ነው። የቅድስት ቤተ ክርስቲያን ተግባሯ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ማገናኘት ብቻ ሳይሆን በችግራቸው ጊዜ ቀድማ በመድረስ መርዳት መሆኑን መረዳት ይገባል።

ቤተ ክርስቲያን ችግረኞችን ከረኃብና ከጊዜያዊ ችግር ነፃ እንዲወጡ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አጽናንታ በገጠማቸው ጊዜአዊ ችግር ሳይሸነፉ ነገ ታላቅ ደረጃ ሊደርሱ እንደሚችሉ ጭምር መንፈሳቸውን ማነቃቃትም እስከ አሁን ከተሠራው የበለጠ ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባው ክርስቲያናዊ ተግባር መሆኑን ክርስቲያኖች ሁሉ እንረዳ። ስለዚህ የገንዘብ ችግር ብቻ ሳይሆን የሥነ ልቡና ስብራት የገጠመውንም በመንፈሳዊ ምክር መርዳት ጊዜ የማይሰጠው መሆኑን መረዳት ይገባል። የቤተ ክርስቲያን ብርሃንነት ለአሕዛብ ከሚገለጥበት ይህ ነውና።

ከክርስቲያናዊ ሥነ ምግባራዊ ተግባራት አንዱ  ለችግር የተጋለጡትን ለመርዳት ቀድሞ መገኘት ነው። ማኅበራት፣ መምህራነ ወንጌል፣ ዘማርያንና ምእመናን ሁሉ እየተባበሩ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለአደጋ የተጋለጡትን ሁሉ በመርዳት ለወገን ደራሽነታቸውን፣ ከራሳቸው ይልቅ ሌሎችን የሚያስቀድሙ መሆናቸውን ካስመሰከሩ የቤተ ክርስቲያን ብርሃንነት ለአሕዛብ ሁሉ እንዲገለጥ ያደርጋል። እንዲህ ማድረጋችንም "ተርቤ አብልታችሁኛልና፣ ተጠምቼም አጠጥታችሁኛልና፣ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፤ ታርዤ አልብሳችሁኛልና፣ ታምሜም ጠይቃችሁኛል፣ ታስሬም ወደ እኔ መጥታችሁ ጠይቃችሁኛልና" ተብለው ከሚመሰገኑትና ወደ ዘለዓለም ሕይወት ግቡ ከሚባሉት ወገኖች ጋር አንድ ያደርገናል። በምድርም የአእምሮ ሰላም እንደምናገኝ አስበን ምክንያት ሳናበዛ ሰውን ሁሉ ለመርዳት ጊዜ ሳንወስድ ተግባራዊ ሥራ መሥራት ችግሩ እንዲቀንስ ስለሚያደርግ ተባብረን ወገኖቻችንን ከችግር በመታደግ ለተቸገረ የሚደርስ ብፁዕ ነው የተባለውን አማላካዊ ቃል በተግባር መግለጥ እንደሚገባ ማስገንዘብ እንወዳለን። ☩

# አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ

**ዲ/ን ተስፋዬ ምትኩ**

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ስለ ዕለት ጉርስና ስለ ዓመት ልብስ እንዳንጨነቅ፣ ብሎም በሕይወታችን ተስፋ እንዳንቆርጥ “ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን? ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይሹታልና፤ ለእናንተ ግን ሰማያዊ አባታችሁ ይህን ሁሉ እንድትሹ ያውቃል” ካለ በኋላ እኛ ከአሕዛብ ተለይተን ልናስበው የሚገባንን መሠረታዊ ጉዳይ ሲነግረን “እናንተስ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል” ብሏል (ማቴ. ፮፥፴፩-፴፫)።

አስቀድማችሁ የሚለው ቃል ምድራዊውን ትታችሁ ሰማያዊውን ብቻ አስቡ ማለት አይደለም። ማስቀደም ስንልም አንደኛ የቅደም ተከተልን ጉዳይ ይመለከታል። ሁለተኛ ደግሞ የአስፈላጊነትን ጉዳይ ይመለከታል። አንድ ተግባር በምንም ዓይነት ምክንያት ሳይከናወን መቅረት የለበትም ብለን ካመንን ከሁሉ አስቀድመን እርሱን እንተገብራለን። ከመጀመሪያው ይልቅ አስፈላጊነቱ ዝቅ ያለውን ተግባር እናስከትላለን። አስፋላጊነቱ በጣም ዝቅ ያለውን ደግሞ ከሁሉ በስተመጨረሻ እናከናውናለን። በቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተምህሮም ከሁሉ ቅድሚያ መስጠት የሚገባን ለሰማያዊው ነው። ይህ ማለት ግን የምንኖርለት ዋናው ዓላማ ሰማያዊቷን ርስት ለመውረስ በመሆኑ ሰማያዊውን ማስቀደም አለብን ማለታችን እንጂ ለምድራዊ ሕይወት አናቅድም፤ አናስብምም ማለት አይደለም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ ዘለዓለማዊ ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንፃ እንዳለን እናውቃለን›› ብሏል (፪ኛ ቆሮ.፭፥፩)።

ሐዋርያው ድንኳንና ቤት ያላቸው ምድራዊና ሰማያዊ ሕይወትን የሚገልጹ ነገሮችን ነው። ምድራዊ ሕይወታችንን በድንኳን ሲመስለው ሰማያዊውን ደግሞ በሕንፃ መስሎታል። ብዙ ጊዜ ድንኳን የሚተከለው ለሰርግ፣ ለልቅሶ፣ ለስብሰባ፣ ለግብዣና ለመሳሰሉት ጊዜያዊ ጉዳዮች ነው። ድንኳን መትከል ቀላል በመሆኑ ጠዋት ምንም ባልነበረበት ቦታ ከሰዓት ድንኳን ተተክሎ ልናየው እንችላለን፤ በተቃራኒው ጠዋት ትልቅ ድንኳን ባየንበት ቦታ ከሰዓት ምንም ላይኖር የሚችልበት አጋጣሚም አለ። ምክንያቱም ድንኳን ቋሚ ያልሆነ ነገር ነውና። ቅዱስ ጳውሎስም ምድራዊ ኑሯችንን በድንኳን የመሰለው ጊዜያዊ በመሆኑ ነው። ቅዱስ ያዕቆብም “ሕይወታችሁ ምንድ ነው? እናንተማ ላንድ ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንደጢስ አይደላችሁምን” (ያዕ. ፬፥፲፬) በማለት የገለጠው ምድራዊ ሕይወትን የሚመለከት ነው።

ስለዚህ ክርስቲያኖች ድንኳን ለተባለው ለምድራዊ ሕይወታቸው በማሰብ እግዚአብሔር በረዳቸው መጠን መትጋት ያለባቸው መሆኑ አልተከለከለም። በዋናነት ማሰብም፣ መትጋትም የሚገባቸው ለሰማያዊ ቤታቸው ነው ለማለት ነው። በተጨማሪም ክርስቲያን በምድር ላይ መልካም ሥነ ምግባር አለኝ ብሎ መመካት የለበትም። ድንኳን ጠዋት ታይቶ ከሰዓት እንደማይገኝ ሁሉ ጠዋት መልካም ሠርቶ ከሰዓት ሊያጠፋ ይችላልና። ቅዱስ ጳውሎስም ምድራዊውን በጊዜያዊ ድንኳን ሲመስለው የሰማዩን ደግሞ በሕንፃ የመሰለበት ምክንያት ዕቅዳችንም በዚያው መጠን እንደሚለያይ ለማሳሰብ ነው። ምክንያቱም ትንሽ ጊዜ ለሚተከለው ድንኳንና ዘመናት ለሚጠይቀው የሕንፃ ሥራ እኩል ዕቅድ ሊኖረን አይችልምና።“አስቀድማችሁ መንግሥቱንና ጽድቁን ሹ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል ተብለናልና”። መንግሥቱንና ጽድቁን አስቀድሙ ሲለን ምድራዊ ዕቅዳችንን ብቻ በመከተል ወደ ዘለዓለማዊ የሕይወት ግባችን የሚያደርሰንን የጽድቅ መንገድ ስተን እንዳንጠፋ ለማስጠንቀቅ ነው። ስለሆነም አንድ ክርስቲያን የሚያከናውናቸው ተግባራት ሦስት ነገሮችን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

**እግዚአብሔር ቢፈቅድ ብሎ መጀመር፡** - አንድ ሰው ጉዞ ከመጀመሩ በፊት የሚደርስበትን ቦታ፣ ከቦታው ከደረሰ በኋላም የሚያደርገውን ነገር፣ ከድርጊቱ የሚገኘውን ውጤት፣ በውጤቱ የሚያገኘውን ጥቅም መረዳት አለበት።ሰው ስኬታማ የሚሆነው ዕቅዶ እንደተነሣበት አሳብ ውጤቱም ተመሳሳይ ከሆነለት ብቻ ነው። ያለበለዚያ ግን ‹‹መነሻውን የማያውቅ መድረሻውን አያውቅም›› እንደሚባል መንገደኛ ሆኖ ይቀራል።

እንደ ክርስትናም በዚህ ምድር ጥረን፣ ግረን የዕለት ጉርስ፣ የዓመት ልብስ አግኝተን ብሎም ለወገን፣ ለሀገር ለቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ሀብትና ንብረት አፍርተን ለመኖር ማቀድ የሚበረታታ እንጂ የሚያስነቅፍ አይደለም። ዕቅዳችን ግን ሕገ እግዚአብሔርን የሚቃረን መሆን የለበትም። ያሰብነውን ለማግኘትም ቢሆን የእኛን ጉልበት፣ ዕውቀት፣ ሀብትና ሌሎች ምቹ ሁኔታዎች ብቻ ሳይሆን ‹‹እግዚአብሔር ቢፈቅድና ብንኖርም›› የሚለውን የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብን አሳብ መሠረት አድርገን መጀመር ይገባናል (ያዕ. ፬፥፲፭)።

“እግዚአብሔር ቢፈቅድ” የሚለውን በሁለት መንገድ መረዳት ይኖርብናል። የመጀመሪያው ልንሠራ ያሰብነው እግዚአብሔር ጥረህ ግረህ ሕይወትህን ምራ ያለውን ትእዛዝ መሠረት ያደረገ ነው ወይ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ይኖርብታል። ሁለተኛው የሚጠቅመውንና ለሕይወታችን የሚበጀውን እግዚአብሔር

ስለሚያውቀው እኛ ስናቅድ እግዚአብሔር ለእኛ የሚያስበውና እኛ ያቀድነው ላይስማማ ስለሚችል እኛ ስላቀድነው ብቻ ስለማንሠራው እግዚአብሔር ቢፈቅድ እንላለን።

ብንኖር የሚለው ደግሞ የምናቅደው ሠርተን ስኬታማ ለመሆን ነው። ያቀድነውን አከናውነን፣ የተመኘነውን ለማግኘት ደግሞ በሕይወትና በጤና መኖር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። የመኖራችን ዋስትና ግን በእግዚአብሔር እጅ የተያዘ ነው። ካልኖርን መሥራትም ሆነ ያሰብነውን ማሳካት ስለማይቻል ‹‹ብንኖር›› ብለን እንጀምራለን። ሌላው ብንኖር ቢፈቅድልንም ስንል ጀምረን እንዳንተወው፣ ሩጠን ባዶ እጃችንን እንዳንመለስ፣ አብበን ያለ ፍሬ እንዳንረግፍ፣ ቸርነቱን ተማፅነን፣ ፈቃዱን ጠይቀን እንጀምራለን ማለታችን ነው። "ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም" ተብለናልና(ዮሐ. ፲፭፥፭)።

**ሕገ እግዚአብሔርን መሠረት አድርጎ ማከናወን፡-** መንገድ ስንጓዝ መድረሻችንን አምነን እንደምንነሣ ሁሉ ከየት ተነሥተን በየት አድርገን፣ በምን ፍጥነት፣ እንዴት ባለው አካሔድ፣ ተጉዘን ከቦታው እንደምንደርስ የሚያሳይ ዝርዝር ማዘጋጀት የግድ ነው። ይህም ዕቅድ የምንለው ነው። እንደ ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ አስተምህሮ ደግሞ የመንገዳችን መመሪያ ሕገ እግዚአብሔር ነው። ሕገ እግዚአብሔርን መሠረት አድርገን ካልተጓዝን እንደ ሕዝበ እስራኤል መንገዱ ይረዝምብናል፤ ካሰብንበት ሳንደርስ የተመኘነውን ውጤት ሳናይ፤ ከፍሬውም ቀምሰን ሳናጣጥም፣ በመንገድ ዘመናችን ያልቅብናል። በምድር ተንከራታች በሰማይም ተሰፋ ቢስ ሆነን እንቀራለን።

ሕዝበ እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ መዳረሻ ግብ ነበራቸው። ይኸውም ከባርነት ነፃ ወጥተው ማርና ወተት ወደምታፈልቀው ከነዓን መድረስና በአባታቸው ርስት፣ በነፃነት፣ በተድላና በደስታ መኖር ነበር። ሆኖም የአካሔዱን ሥርዓት አላወቁም፤ መሪያቸውን ሙሴን አልታዘዙም፤

ተማሪ ኮርጆ ውጤታማ ለመሆን መሞከር፣ ገበሬ ከነእንክርዳዱ ሸጦ ለመበልጸግ ማሰብ፣ ነጋዴ በሚዛን ማጭበርበር፤ አምራቾች የዕቃን ጥራት ቀንሰው ማምረት በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዓለማዊ ሕግም ያስጠይቃል።

ከእርሱ ይልቅ በፈርኦን ፊት ድንቅ ተአምራት ሠርቶ ባሕረ ኤርትራን እንደ ግድግዳ አቁሞ ያሻገራቸውን እግዚአብሔርን፤ ምንም በሌለበት ምድረ በዳ ከሰማይ መና አውርዶ፤ ከደረቅ ዐለት ውሃ አፍልቆ፤ ያጠገባቸውን አምላካቸውን ትተው በወርቅ የተሠራ ምስል አመለኩ፤ እርም የሆነውን የሰናኦር ካባ ለበሱ፤ ከአሕዛብ ጋር በዝሙት ወደቁ፤ በዚህም ተቀሰፉ፤ በ፵ ቀን ይደርሱት የነበረው መንገድ ፵ ዘመን ፈጀባቸው፡፡ በረሓ ለበረሓ ሲንከራተቱ እባብ እየነደፋቸው፣ የውኃ ጥም እየፈጃቸው ከነዓን ደርሰው ከፍሬው ሳይቀምሱ በመንገድ ሞተው ያለቁ ብዙ ናቸው፡፡ ከኢያሱና ከካሌብ በቀር ልጆቻቸው እንጂ እነርሱ ርስታቸውን አይተው አልወረሱም፡፡

ቤተ ክርስቲያን የእራኤላውያን ታሪክ መሠረት አድርጋ ያቀድነውን ከግብ ለማድረስ ስንነሣ አካሔዳችን ሕገ እግዚአብሔርን ማእከል ያደረገ እንዲሆን ትመክረናለች፡፡ ለዚህም ቅዱስ ዳዊት‹‹ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው›› በማለት ያመሰገነውን ለመንገዳችን መሪ እንድናደርግ ታሳስበናለች(መዝ. ፻፲፰፥፻፭)፡፡ በአቋራጭ ስኬታማ ለመሆን ሕገ ወጥ ተግባር እንዳንፈጽም ታስጠነቅቀናለች፡፡ ተማሪ ኮርጆ ውጤታማ ለመሆን መሞከር፣ ገበሬ ከነእንክርዳዱ ሸጦ ለመበልጸግ ማሰብ፣ ነጋዴ በሚዛን ማጭበርበር፤ አምራቾች የዕቃን ጥራት ቀንሰው ማምረት በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በዓለማዊ ሕግም ያስጠይቃል፡፡ የቤተ ክርስቲያንን አሥራት፣ የመንግሥትን ግብር ማጓደል የተከለከለ ነው፡፡ "የቄሣርን ለቄሣር፣ የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር ስጡ" ተብሏልና (ማቴ. ፳፪፥፳፩)፡፡ በትክክለኛ መንገድ ብቻ ሠርቶ ካሰበበት ለመድረስ መትጋት "ጥረህ ግረህ ብላ" የተባለውን ትእዛዝ መፈጸም በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንን ደስ ያሰኛታል፡፡ ክርስቲያኖች የሚያቅዱት ከሌሎች ዕቅድ የሚለየውም በዚህ ነው፡፡

**ሁሉ ለበጎ ነው ብሎ መቀበል፡-** አምላካችን እግዚአብሔር ደግ አባት በመሆኑ ለልጆቹ የሚበጀውን ይሰጠናል፡፡ "ለእናንተ የማስባትን አሳብ እኔ አውቃለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ ፍጻሜና ተስፋ እሰጣችሁ ዘንድ የሰላም አሳብ ነው እንጂ የክፉ ነገር አይደለም" (ኤር.፳፱፥፲፩) የተባለው ለዚህ ነው፡፡ እኛም ለሕይወታችን ምን እንደሚያስፈልገን ለይተን የምንሻውን ለማግኘት የሚጠበቅብንን ኃላፊነት ለመወጣት ዐቅደን፣ ዕቅዳችንንም ለማሳካት የተቻለንን ጥረት ካደረግን የመጨረሻውን ውጤት ለእግዚአብሔር መተው ይገባናል፡፡ እግዚአብሔር ለጥረታችሁ የሚገባው ይህ ነው ብሎ ከሰጠንም አንተ ያልከው ይሁን ብለን በደስታ እንቀበላለን፡፡ ብዙዎቻችን ግን እግዚአብሔር የሰጠንን ንቀን የራሳችንን ውሳኔ ተግባራዊ ለማድረግ ከእግዚአብሔር ጋር ክርክር ውስጥ እንገባለን፡፡ ይህ ክርክርና ጭንቀት የእግዚአብሔርን አሳብ ሊያስቀይር እንደማይችልም ጌታ ሲናገር "ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?" ብሎናል (ማቴ. ፮፥፳፯)፡፡

‹‹ሁሉ ለበጎ ነው›› ብለን መቀበል አለብን ስንል ዓላማቸውን ከግብ ለማድረስ ጉዞ ጀምረው ትንሽ ፈተና ሲያጋጥማቸው "እግዚአብሔር ስላልፈቀደልኝ ምንም ማድረግ አልችልም" ብለው ተስፋ እንደሚቆርጡት ደካሞች ስንፍናችንን በፈቃደ እግዚአብሔር ማላከክ የሌለብን መሆኑንም መረዳት ይኖርብናል፡፡ ሰው በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊ ሕይወቱ የተሻለ ለመሆን ሲነሣ ፈተና ያጋጥመዋል፡፡ የሰው ልጅ በዕቅድና በዓላማ ሲጓዝ፣ ሁል ጊዜ በሥራ ይጠመዳል፤ በሥራ የተጠመደ ሰው ደግሞ ከኃጢኣት ይርቃል፡፡ ለሕይወቱ የሚያስፈልገውንም ያገኛል፡፡ ካገኘው ገንዘብ ለቤተ ክርስቲያን አሥራት ያወጣል፤ ለድሆች ምጽዋት ይሰጣል፡፡ በዚህም በሕይወቱ ደስተኛ ሆኖ ይኖራል፡፡ ድርጊቱ ግን ጠላት ሰይጣንን ደስ ስለማያሰኘው ያሰበውን እንዳይሠራ መሰናክል ይፈጥርበታል፡፡ ሥራ በመተው እንዲደኸይ፣ በድህነቱም እግዚአብሔርን እንዲያማርር፣ በሕይወቱ ተስፋ ቆርጦ ሞትን እንዲመኝ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ ክርስቲያኖች ስኬታማ ለመሆን ስንተጋ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች ሳንጋፈጥ ፈቃደ እግዚአብሔር አይደለም በሚል ብቻ መተው ለሰይጣን እጅ መስጠት መሆኑን መረዳት ይገባናል፡፡ በጉዟችን ችግር ሲያጋጥመን በእኔ ስንፍና ወይስ በዲያብሎስ ተንኮል የሚለውን መመርመር ከእኛ ይጠበቃል፡፡

ዕቅዳችን ቢሳካ እንኳ እግዚአብሔር በሚፈቅደው መንገድ ሠርተን ማግኘት አለማግኘታችንን መመርመር ይጠበቅብናል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ‹‹ጥረህ ግረህ በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ›› ይለናል፡፡ ስለሆነም ስኬታችን የድካማችን ውጤት ነው ወይስ ሌሎች የደከሙበትን በኃይል፣ በሥልጣን፣ በማታለል ወስደንባቸዋል? የሚለውን መመርመር ከተደጋጋሚ ስሕተት ያድነናል፡፡

በአጠቃላይ በዚች ምድር ብንኖርም የዛሬው ኑሯችን ጊዜያዊ እንጂ ዘለዓለማዊ አይደለምና ለጊዜያዊው ሳይሆን ለዘለዓለማዊው፣ ለምድራዊው ሳይሆን ለሰማያዊው፣ ለሥጋዊው ሳይሆን ለመንፈሳዊው ዋጋ እየተጋን መኖር ይገባናል፡፡ ቅድሚያ መስጠት ላለብን ጉዳይ ቅድሚያ እንስጥ ስለተባለ ምድራዊውን መተው አይገባም፡፡ የተለየ ጸጋ ከሌለን በቀር ሳንበላ፣ ሳንጠጣ መኖር አንችልምና፡፡ እርሱንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ አስቀድመን በቸርነቱ እንደሚሟላልን ተስፋ አድርገን ልንንቀሳቀስ ይገባል፡፡ ያሰብነውን ተግባራዊ ለማድረግ እግዚአብሔር በቸርነቱ፣ ድንግል ማርያም በአማላጅነቷ፣ ቅዱሳን በተራዳኢነታቸው አይለዩን፡፡ አሜን!! ⌖

# ናሁ እግዚአብሔር ይነብር ዲበ ደመና ቀሊል ወይመጽእ ውስተ ግብፅ

(ኢሳ.፲፱፥፩)

**ቀሲስ ዐቢይ ሙሉቀን**

የቃሉ ተናጋሪ ነቢዩ ኢሳይያስ ሲሆን እግዚአብሔር አምላክ ወደ ግብፅ ስለ መሰደዱ ገልጾለት የተናገረው ነው። ሙሉ ቃሉ "ናሁ እግዚአብሔር ይነብር ዲበ ደመና ቀሊል ወይመጽእ ውስተ ግብፅ፤ ወያድለቀልቅ ግብረ እደዊሆሙ ለግብፅ እምቅድመ ገጹ፤ እነሆ እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይመጣል፤ የግብፅም የእጆቻቸው ሥራዎች በፊቱ ይዋረዳሉ፤ የግብፃውያንም ልብ በውስጣቸው ይቀልጣል" ይላል። ነቢዩ በዚህ ምንባብ ስለሚሔድበት ሀገርና ስለሚሔድበት ምክንያት ተናግሯል።

በነቢዩ አድሮ "ሰማይ ዙፋኔ ነው፤ ምድርም የእግሬ መረገጫ ናት፤ የምትሠሩልኝ ቤት ምን ዓይነት ነው? የማርፍበትስ ስፍራ ምንድን ነው?" (ኢሳ.፷፮፥፩) ብሎ የተናገረ አምላክ፣ በሠለስቱ ምእትም "አልቦ አመ ኢሀሎ ወአልቦ አመ ተኃጥአ ወአልቦ አመ አስተረአየ ፍጹመ በመለኮቱ፤ አልቦ ዘይክል ርእዮቶ ወአልቦ ዘየአምር ዘከመ እፎ ህላዌሁ፤ የሌለበት ጊዜ የለም የታጣበትም ጊዜ የለም በመለኮቱ ግን ፈጽሞ የታየበት ጊዜ የለም። እርሱን ማየት የሚችል የለም አነዋወሩም እንደምን እንደሆነ የሚያውቅ የለም" (ቅዳሴ ሠለስቱ መእት) ተብሎ የተነገረለት፣ በጊዜና በቦታ የማይወሰነው፣ አነዋወሩን ከእርሱ በቀር ማንም የሚያውቀው የሌለው አምላክ በተዋሐደው ሥጋ ተቀመጠ፣ ሔደ፣ ተሰደደ፣ ተራበ፣ እየተባለ ይነገርለታል።

በዚህ ምክንያት ነቢዩ በባሕርዩ የማይመረመረው አምላክ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ የፈጸመው የድኅነት ተግባር አስቀድሞ በትንቢት መነጽር ተገልጾለት የሚሔድበትን ቦታ ለምን ተግባር እንደሚሔድ ነገረን። በዚህ ቦታ ይኖራል፣ በዚህ ቦታ ደግሞ አይኖርም የማይባለው አምላክ በደመና ላይ ተቀመጠ መባሉ በተዋሐደው ሥጋ ሊሠራው ያሰበውን መናገሩን ያስገነዝባል። እግዚአብሔር በዚህ አለ፣ በዚህ ደግሞ የለም የማይባለው አምላክ ልገለጥ ባለ ጊዜ እሱ በወደደው ይገለጻል። ሊቃውንቱ እንደሚያስረዱት ደመና የልዕልናው መገለጫ ነው። በትርጓሜ ወንጌልም "ዘበእንተ ዕበይከ ትትሜሰል በደመናት፤ ስለ ልዕልናህ በደመናት ትመሰላለህ" ተብሎ ተገልጿል(ማቴ. ፮፥፱ አንድምታ) ።

ደመና የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫና መመላለሻው መሆኑን ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ "ዘይጠፍር በማይ ጽርሖ፤ ወረሰየ ደመና መከየዶ፤ ዘየሐውር በክነፈ ነፋስ፤ ዕልፍኙን በውኃ የሚሠራ፣ ደመናን መሔጃው የሚያደርግ፣ በነፋስ ክንፍም የሚሔድ" (መዝ.፻፫፥፫) በማለት ማድነቁን እናነባለን። ከዚህ ቃል የምንረዳው አምላክ ምንም የሚሳነው ነገር የሌለ መሆኑን ነው። ዕልፍኙን በውኃ ይሠራል ሲባልም በዕልፍኝ ውስጥ ይቀመጣል ማለት አይደለም። ይህም አምላካችን ከመመርመር በላይ መሆኑን፣ ዕፁብ በማለት ብቻ የሚታለፍ መሆኑን የሚያስገነዝብ ቃል ነው። ሊቁ ቅዱስ ያሬድም ስለዕርገቱ በተናገረበት ድርሰቱ "ዐርገ ሰማያተ በዐምደ ደመና፣ ለድንግል ዘፈትሐ ማኅፀና፣ ለደቂቀ እስራኤል ዘአውረደ መና...፤ ለእስራኤል ልጆች መናን ያወረደ፣ ድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና እንድትወልደው ያደረገ፣ በደመና ዓምድ ወደ ሰማይ ዐረገ" በማለትረ አድናቆቱን ገልጧል (ዝማሬ ዘዕርገት)። በደመና ዐምድ ዐረገ የሚለውም በባሕርይ ክብሩ ሲል ነው።

የእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ የተባለውን ደመና ሊቃውንት በብዙ መልኩ ተርጒመውታል። የኢሳይያስን ትንቢት የተረጐሙ ሊቃውንት "በፈጣን ደመና ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይመጣል" የሚለውን "በሙሴ፣ በአሮን፣ በኤርምያስ፣ በማርቆስ አድሮ፣ በዘባነ ማርያም ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይመጣል" ብለው ተርጒመውታል (ኢሳ.፲፱፥፩ አንድምታ)። ራእየ ዮሐንስን የተረጐሙ ሊቃውንትም "ናሁ ይመጽእ በደመና ሰማይ፤ እነሆ በሰማይ ደመና ይመጣል" የሚለውን ሲተረጒሙ በጎ በሆኑ መምህራን አድሮ ክፉዎችን ነገሥታት ለመዝለፍ፣ ለመንቀፍ ይመጣል፤ በኤልያስ አድሮ አክአብን፣ በዮሐንስ መጥምቅ አድሮ ሄሮድስን እንደዘለፈው ማለት ነው።

በጎ በጎዎችን መምህራን ደመና አላቸው ከውቅያኖስ ዝናም ቋጥሮ ወጥቶ እየዞረ እያዘነመ ለብዙ አዝርእት፣ አትክልት ይጠቅማል፣ በጎ በጎዎቹ መምህራንም ዓለምን ዙረው አስተምረው፣ ያልተመሰለውን መስለው፣ የተመሰለውን ተርጒመው ብዙ ምእመናንን መጥቀማቸውን መናገር ነው። በዚሁ አንድምታ ደመና የተባለች እመቤታችን ድንግል ማርያም እንደሆነችም ያስረዳል (ራእ. ፩፥፯ አንድምታ)። ከላይ ከተጠቀሰው ትንታኔ በመነሣት ደመና የተባሉ ነቢያት፣ ሐዋርያትና ድንግል ማርያም መሆናቸውን መረዳት ይቻላል። ምሥጢሩን አንባብያን እንዲረዱት እያንዳንዱን ጉዳይ በአጭሩ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

**ሀ. ነቢያት፡-** ደመና ዝናምን ተሸክሞ ወደ ሰማይ ይወጣና መልሶ ወደ መሬት ይልካል። ነቢያትም ነቢዩ ዳዊት "ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ" (መዝ.፻፲፰፥፻፫) በማለት የተናገረለትን የእግዚአብሔርን ቃል ተቀብለው ወደ ሕዝበ እስራኤል ሲያደርሱ ኖረዋል። ደመና የሚያስከትለው ዝናምን፣ ዝናቡም ልምላሜን፣ ተስፋን ነው። ነቢያትም በትንቢታቸው ንጹሕ ዝናም የተባለው ጌታ ይወርዳል፤ ይወለዳል እያሉ በተናገሩት ትንቢት የሕዝቡን ተስፋ ሲያለመልሙ ኖረዋል። ነቢያት እግዚአብሔር እንዲህ አለ

እያሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ የሚያደርሱ ስለሆኑ ደመና ተብለዋል። ነቢዩ ኢሳይያስ "እግዚአብሔር በደመና ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይሔዳል" ሲል በነቢያቱ አድሮ የግብፅን ሕዝብ ያስተምራል። ሕዝበ እስራኤልን ከመከራ ሥጋ፣ ከመከራ ነፍስ ይታደጋል ማለቱ ነው።

**ለ. ሐዋርያት፡-** ኋላም በደመና በተመሰሉ ሐዋርያት ላይ አድሮ ሕዝቡን ሊያስተምር ወደ ግብፅ እንደሚሔድ፣ በሐዋርያው በቅዱስ ማርቆስ ላይ አድሮ በግብፅ የነበረውን አምልኮተ ጣዖት አጥፍቶ፣ ኢአማንያን የነበሩትን እያስተማረ ከክህደት ወደ እምነት፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ ሲመልሳቸው መኖሩን መናገር ነው። ሐዋርያት በደመና መመሰላቸው ቃሉን ይዘው ወደ አሕዛብ ሁሉ ገብተው ሲያስተምሩ በመኖራቸው ነው።

**ሐ. ድንግል ማርያም፡-** እግዚአብሔር በደመና ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይሔዳል በማለት ነቢዩ የተናገረው ለጊዜው እግዚአብሔር በነቢያት፣ በሐዋርያት አድሮ አምላካዊ መግቦቱን፣ ጥበቃውን፣ ሀልዎቱን፣ ቸርነቱን የሚገልጽ እንደሆነ ለማስርዳት ሲሆን ፍጻሜው ግን በድንግል ማርያም ጀርባ ታዝሎ ወደ ግብፅ እንደሚሰደድ መናገሩ ነው። ነቢዩ ደመና ያላት ልጇን ወዳጇን በጀርባዋ አዝላ በረሓ ለበረሓ የተሰደደችውን ድንግል ማርያምን ነው። ነቢያት በትንቢታቸው እመቤታችንን በደመና፣ ልጇን ኢየሱስ ክርስቶስን ደግሞ በዝናም እየመሰሉ አስተምረዋል። ሐዋርያት በስብከታቸው፣ ሊቃውንት በትርጓሜአቸው ለዓለም አድርሰውታል።

ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም "አንቲ ዘበአማን ደመና እንተ አስተርአይኪ ለነ ማየ ዝናም፤ የዝናም ውኃ የታየብሽ የእውነት ደመና አንቺ ነሽ" በማለት ገልጧታል (ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ) ። ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም የዝናም ውኃ የታየብሽ የእውነት ደመና አንቺ ነሽ በማለት የተናገረውን ሊቃውንቱ ሲተረጒሙ እርሷን ደመና ልጇን ደግሞ ዝናም ይሉና እውነተኛ አላት የድንግል ማርያም አማላጅነቷ የማይታበል ነውና ብለው አመሥጥረውታል። በዚህ ምክንያት እመቤታችን እውነተኛ ደመና ተብላለች። እውነተኛ ደመና ደግሞ ታይቶ የማይቀር ከእርሱ የሚጠበቀውን ዝናም የሚያስገኝ ነው። ድንግል ማርያምም ጥንት ከአዳም ጀምሮ የመዳን ተስፋ የነበረች፣ የአዳም የመዳን ተስፋ የተፈጸመውም እውነተኛውን የምሕረት ዝናም ኢየሱስ ክርስቶስን ስለወለደችልን ነው።

አባ ጽጌ ድንግል "ቀስተ ደመና ማርያም ትእምርተ ኪዳኑ ለኖኅ፤ ዘእግዚአብሔር ሤመኪ ለተዝካረ ምሕረት ወፍትሕ፤ ህየንተ ቀሰፋ ለምድር ወአማሰና በአይህ፣ በእንቲአኪ አሠርገዋ በጽጌ ኵሉ አቅማህ፤ ከመ በከዋክብት አሠርገዎ ለሰማይ ስፉሕ፤ ምድርን ስለቀጣትና በንፍር ውኃ ስለአጠፋት የእውነተኛ ፍርዱና የምሕረቱ መታሰቢያ አድርጎ እግዚአብሔር የሾመሽ የኖኅ የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና ማርያም አንቺ ነሽ። ሰፊ የሆነ ሰማይን በከዋክብት እንዳስጌጠው ሁሉ ምድርንም ስለአንቺ በአበባዎች ሁሉ አሸብርቋታል" በማለት እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ ምልክት ትሆን ዘንድ ለአባታችን ለኖኅ በሰጠው ምልክት መስሏታል።

እግዚአብሔር አምላካችን ለአባታችን ለኖኅ ከጥፋት ውኃ በኋላ ዳግመኛ ምድርን በንፍር ውኃ እንዳያጠፋት ቃል ኪዳን ገብቶለታል። "እግዚአብሔር አምላክም ለኖኅ አለው፤ በእኔና በእናንተ መካከል ከእናንተም ጋር ባለው በሕያው ነፍስ ሁሉ መካከል ለዘለዓለም ትውልድ የማደርገው የቃል ኪዳኔ ምልክት ይህ ነው፤ ቀስቴን በደመና አኖራለሁ፤ የቃል ኪዳኔም ምልክት በእኔና በምድር መካከል ይሆናል። በምድር ላይ ደመናን በጋረድሁ ጊዜ ቀስቴ በደመናው ትታያለች" (ዘፍ.፱፥፲፪-፲፬) ተብሎ የተነገረው የሚገልጠው ይህን ነው።

እግዚአብሔር አምላክ ለኖኅ የገባለትን ቃል ኪዳን እንደሚያጸና ምልክት ይሆነው ዘንድ የሰጠው ቀስተ ደመና ነው። ይህቺ የቃል ኪዳን ምልክት የሆነችው ቀስተ ደመና ደግሞ እምቤታችን ድንግል ማርያም እንደሆነች ሊቁ የኖኅ የቃል ኪዳኑ ምልክት ቀስተ ደመና አንቺ ነሽ እያለ ያመሰግናታል። ሊቁ አባ ጽጌ ድንግል እመቤታችንን ባመሰገነበት ድርሰቱ "በደመና ሰማይ ተፅዒኖ ከመ ዘኢየአምር ኑሶሳወ፤ እንዘ ይወርድ ውስተ ምድረ ግብፅ ደኪሞ ሐፌወ፤ ወሥነ ከናፍሪሁ ጽጌ በሐሩረ ፀሐይ መጽለወ፤ ለጠቢው ሶበ ፈተወ አጥባተ እሙ ምንተወ፤ ኃጢኦ ሐሊበ ከመ ሕፃናት ለሀወ፤ ህየንተ አንብዑ ለወልድ ለእኩን ክዕወ፤ መንቀሳቀስን እንደማያውቅ ሁሉ በሰማይ ደመና ተጭኖ ወደ ምድረ ገብፅ ሲወርድ ደክሞት አላበው፤ የከንፈሮቹ ውበትም በፀሐይ ሐሩር ጠወለገ፤ ከሁለቱ የእናቱ ጡቶች ሊጠባ በወደደ ጊዜ ወተት አጥቶ እንደ ሕፃናት አለቀሰ፤ ስለ ዕንባው ፈንታ እኔ ፍስስ ልበል። (ሰቈቃወ ድንግል) ብሎ እንደገለጸው እግዚአብሔር በደመና ተጫነ፤ ሔደ፤ ተመላለሰ ተብሎ ይነገራል።

አባ ጽጌ ድንግል እንዳመሠጠረው ጌታችን መጀመሪያ ወደ ምድረ ግብፅ ሲሰደድ በደመና ተጭኖ እንደሔደ ይናገራል። ሲሰደድም በግብፅ በረሃ የደረሰበትን ውኃ ጥም፣ የበረሃውን ቃጠሎ፣ በረሃብ ያለች እናት ማጥባት አይቻላትምና ሊጠባ የወደደውን ጡት አማናዊት ደመና ከተባለች ድንግል ማርያም ማግኘት እንዳልቻለ፣ በተዋሐደው ሥጋ የደረሰበትን መከራ ሁሉ በእምነት መነጽር በመመልከት እኛም በእምነት መነጽር እንድንመለከተው ይጋብዘናል።

እግዚአብሔር አምላክ በባሕርየ መለኮቱ የሌለበት ቦታ ኑሮ ከነበረበት ወደ ሌለበት ቦታ ሔደ አይባልም። ነገር ግን አስቀድሞ በነቢያት አድሮ ትንቢት ሲያናግር ሕዝቡን ሲያስተምር እንደኖረ በኋላም ከድንግል ማርያም በኀቱም ድንግልና ተፀንሶ በኀቱም ድንግልና ተወልዶ በኃጢአቱ ምክንያት የተሰደደ አዳምን በስደቱ ለመካስ በአማናዊት ደመና በድንግል ማርያም ጀርባ ታዝሎ ሸሸ። አንድ መንገደኛ ሰው የሚሔድበት ሀገርና የሚሔድበት ምክንያት ይኖረዋል። የሚሔድበትን ሀገር ነቢዩ ኢሳይያስ በስም ጠቅሶ ወደ ግብፅ መሆኑን ነግሮናል። ነቢዩ ሆሴዕም "ልጄን ከግብፅ ጠራሁት" (ሆሴዕ ፲፩፥፩) በማለት ትንቢት ተናግሮ ነበርና በኋላ ጊዜው ሲደርስ በድንግል ማርያም ጀርባ ታዝሎ እንደ

ሕፃናት እየተራበ፣ እየተጠማና እያለቀሰ ወደ ግብፅ ተጓዘ።

**የሔደበት ምክንያት፦** እንኳንስ እግዚአብሔር ሰውም ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ሲንቀሳቀስ ምክንያት አለው። እግዚአብሔር ሰውን በአርያውና በአምሳሉ ሲፈጥር ምክንያት ነበረው፣ ነቢያትን እንዲያስተምሩ ወደ ሕዝቡ ሲልካቸው ምክንያት ነበረው፤ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ከድንግል ማርያም በኅቱም ድንግልና ተፀንሶ በኅቱም ድንግልና ሲወለድ ምክንያት ነበረው፤ ወደ ግብፅ ሲሰደድም ምክንያት ነበረው። ይህ ምክንያት ደግሞ በግብፅ ሠልጥኖ የነበረውን አምልኮ ጣዖት ለማጥፋት ነው።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ "ወያድለቀልቅ ግብረ እደዊሆሙ ለግብፅ እምቅድመ ገጹ፤ የግብፅም የእጆቻቸው ሥራዎች በፊቱ ይርዳሉ፤ የግብፃውያንም ልብ በውስጣቸው ይቀልጣል" (ኢሳ. ፲፱፥፩) በማለት ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ግብፅ የተሰደደበትን ምክንያት ያስረዳል።

**ድንግል ማርያምም ጥንት ከአዳም ጀምሮ የመዳን ተስፋ የነበረች፣ የአዳም የመዳን ተስፋ የተፈጸመውም እውነተኛውን የምሕረት ዝናም ኢየሱስ ክርስቶስን ስለወለደችልን ነው።**

አባ ጽጌ ድንግልም "አብርሂ አብርሂ ናዝሬት ሀገሩ፤ ንጉሥኪ በጽሐ ዘምስለ ማርያም መጾሩ፤ ጣዖታተ ግብፅ ኵሎ ቀጥቂጦ በበትሩ፤ ይጉየዩ ወይትኀፈሩ ሠራዊተ ሄሮድስ ጸሩ፤ ዘበላዕሌሁ እኩየ መከሩ፦ ናዝሬት ሀገሩ እጅግ ደስ ይበለሽ፤ ንጉሥሽ ክርስቶስ ከእናቱ ከድንግል ማርያም ጋር የግብፅን ጣዖታት ሁሉ በበትረ ሥልጣኑ ቀጥቅጦ ተመልሷልና። በእርሱ ላይ ክፉን የመከሩ የጠላቱ የሄሮድስ ሠራዊት ይፈሩና ይሸሹ" (ሰቈቃወ ድንግል) በማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በግብፅ የነበሩ ጣዖታትን አጥፍቶ ሲመለስ ለኢየሩሳሌም የነበረውን ደስታ ያስረዳል።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰደደበት ምክንያት ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በትርጓሜ ወንጌል እንደገለጹት ስደትን ለሰማዕታት ለመባረክ ነው። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ "ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ፤ ከእኔም ተማሩ" (ማቴ. ፲፩፥፳፱) በማለት እንደተናገረው በዚህ ምድር ላይ ልንፈጽመው የሚገባንን ተግባር በሙሉ እርሱ እየፈጸመ አሳይቶናል። በዚህም ምክንያት ገና ሕፃን ሳለ በእናቱ ጀርባ ተቀምጦ ሰማዕታት ሊደርስባቸው የሚችለውን ሁሉ መከራ ተቀበለ። በሕፃንነቱ በግብፅ በረሃ ረሓቡን፣ ጥሙን፣ መከራውን ሁሉ ታግሦ በመዋዕለ ስብከቱም "ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና" (ማቴ. ፭፥፲) በማለት አስተማረ። ምእመናን ስለጽድቅ የሚደርስባቸውን ስደትና መከራ እንዳይሳቀቁት ባርኮ ይሰጣቸው ዘንድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈጣን ደመና በድንግል ማርያም ጀርባ ላይ ተቀምጦ ተሰደደ።

በአጠቃላይ እግዚአብሔር አምላካችን የሌለበት ቦታ ኖሮ ከአለበት ወደ ሌለበት ሔደ የሚባል አይደለም። በሁሉ ቦታ፣ በሁሉ ጊዜ ያለና የሚኖር ምሉዕ በኵለሄ ነው። ይሁን እንጂ አስቀድሞ በአበውና በነቢያት በልዩ ልዩ መገለጫዎች ሲገለጥ መጣ እየተባለ ሲነገርለት ኖሯል። በኋላም በሐዲስ ኪዳን ከሦስቱ አካል አንዱ ወልድ በአጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ወደዚህ ዓለም ሲመጣ በተዋሐደው ሥጋ ተሰደደ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ አለቀሰ ተብሎ ተነገረለት።

የሰውን ልጅ ያድን ዘንድ ወዶና ፈቅዶ የፈጸማቸውን ተግባራትም አስቀድሞ በነቢያት አስነገረ፤ በኋላም እርሱ በተግባር ፈጸመ። የሰውን ልጅ ሊያድን ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ በትንቢቱ የተናገረው ነቢይ ኢሳይያስ "እግዚአብሔር በፈጣን ደመና ተቀምጦ ወደ ግብፅ ይመጣል፤ የግብፅ የእጆቻቸው ሥራዎችም በፊቱ ይርዳሉ" በማለት የተናገረውን በቀጠሮው መሠረት መጥቶ የአዳምን ተስፋ አለመለመ።

የማያደርገውን የማይናገር፣ የተናገረውን የማያስቀር አምላክ በአጭር ቁመጥ በጠባብ ደረት ተወስኖ ፈጣን ደመና በተባለች በድንግል ማርያም ጀርባ ተቀምጦ ወደ ግብፅ ተሰደደ፤ በግብፅ ያሉ ገዳማትን ባረከ፤ ስደትን ለሰማዕታት ባርኮ ሰጠ፤ ከግብፅ ምድር አምልኮ ጣዖትን አጠፋ። ስደትን ለሰማዕታት ባርኮ የሰጠ የምሕረት አምላክ ዛሬም ከእያንዳንዳችን ልቡና አምልኮ ጣዖትን አጥፍቶ ሰማዕታት ያለፉበትን የተጋድሎ ሕይወት በተግባር ፈጽመን የመንግሥቱ ወራሾች፣ የስሙ ቀዳሾች እንዲያደርገን እግዚአብሔር አምላካችን ይፍቀድልን። አሜን!!✥

# የምንሠራው ከሪፖርት ባለፈ ሕይወትን ለመታደግ ይሁን

ዲ/ን አሻግሬ አምጤ

በአገር ላይ መከራ ሲመጣ፣ ሰዎችም ለችግር ሲጋለጡ አካላዊ፣ ሥነ ልቡናዊ እና ሃይማኖታዊ ስብራት እንዳይደርስባቸው ከመሥራት ይልቅ ለሪፖርት እና በተጎጂዎች ችግር ለመታወቅ የሚሠሩት ወገኖች ብዙ ናቸው:: እገሌ ወይም እነእገሌ እንዲህ አደረጉ ለመባል እንጂ ተጎጂዎች ይበልጥ እንዳይጎዱ መጠንቀቅ ከብዙዎች በመራቁ ተጎጂዎች ለተደራራቢ ችግር ሲጋለጡ እንመለከታለን:: አንዳንዶችም ተራ የሒሳብ ስሌት አስመስለው ጨዋታቸውን ቍጥር ላይ ብቻ ያደርጉታል:: እንዲህ አይነቱ ድርጊት ሰዎችን ከማሳወቅ ባለፈ የሚጠቅመው አንዳች ነገር የለም፤ ለተጎጂዎችም ጠብ የሚልላቸው መፍትሔ የለም:: ችግር የገጠማቸውን ወገኖቻችንን ለመርዳት ስንነሣም መጀመሪያ ሰው መሆናቸውን አምነን፣ ስብራታቸው ተሰምቶን፣ ተጨማሪ ኀዘን ላለመፍጠር ተጠንቅቀን መሆን ይኖርበታል:: ሰው ከሆዱ ይልቅ ሰብአዊ ክብሩ ስለሚበልጥበት ልዩ ነገር እንዳደረግን እያሰብን ሳይሆን እግዚአብሔር የሰጠንን ተካፍለን እየበላን መሆኑን አምነን መርዳት ይኖርብናል::

> **በመከራ ውስጥ ቢሆኑም አለመሸበርን ከቀደምቶቹ በተግባር የተማረው ቅዱስ ጳውሎስ ራሱም የቀዳሚዎችን አሠረ ፍኖት ተከትሎ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማን ነው በማለት ተናግሯል::**

ሰሞኑን አንድ አስገራሚ ፎቶ በማኅበራዊ ብዙኃን መገናኛ ሲዘዋወር ሰንብቷል:: ፎቶው ከዓመታት በፊት በደቡብ ሱዳን ተከሥቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት በተፈጠ ረሃብ ጠኔ ይዟት የወደቀችን ልጅ ጆፌ አሞራ አንሥቶ ሊወስዳት ሲቀርባት የሚያሳይ ነው:: የፎቶ አንሺው ጭንቀት የነበረው አሞራው ልጅቷን ከማንሣቱ በፊት ካሜራውን አስተካክሎ ምስሉን ማስቀረት ላይ ነበር:: በወቅቱ የተነሣው ፎቶ አንሺውን ለዓለም አቀፍ ዕውቅና ዳርጎት፣ ሰውዬውም አሳቡ ተሟልቶ ሊሸለም የቀሩት ደቂቃዎች ነበሩ::

ጋዜጠኛው የተቀዋጣለት ፎቶ ያነሣ ሲመስለው የልጅቷን መጨረሻ ሳያይም፣ ሊበላት ከሚያሰፈስፈው አሞራ ሳይታደጋትም አካባቢውን መልቀቁን የሚያውቀው ራሱ ብቻ ነበር:: በጠኔ የወደቀችውን ልጅ ከሞት መታደግ እንዳለበት አላሰበም:: ያሰበው በእርሷ ሞት ታዋቂነትን ማግኘት ነበር::

ፎቶው የብዙዎችን ቀልብ ስቦ ታዋቂነትን ስላተረፈለት የፎቶ ግራፉ አንሺ ለሽልማት ታጭቶ መድረክ ላይ ሲወጣ ታዋቂ በመሆኑ ደስታው ወሰን አጥቶ ነበር:: ፎቶ ግራፉን ያነሣው ሰው በሥራው ታዋቂነትን በማግኘቱ እየተደሰተ ለመሸለም ወደ መድረክ በወጣበት ወቅት ከአንድ ጋዜጠኛ ቀላል የመሰለ ጥያቄ ተጠየቀ:: ጠያቂውም ያነሣኸው ፎቶ የብዙዎቻችንን ቀልብ እንዲስብ አድርገህ በማንሣትህ እናደንቅሃለን:: ግን ልጅቷን ከጆፌ አሞራ ታደግሃት ወይ? አለው:: በዚህ ቅጽበት ወሰን አጥቶ የነበረው የፎቶው ባለቤት ጋዜጠኛ ደስታ ተኖ ጠፋ::ሽልማቱን ተቀብሎ ወደ ቤቱ ቢሔድም ደስታና እርሱ ተለያዩ::

ከዚያ በኋላ ከኀዘን ተዛምዶ ራሱን እየወቀሰ መኖር ቢጀምርም ሰርክ ምስሏ ከፊቱ መጥቶ እየተደቀነ ዕረፍት ሲነሣው ለሽልማት በታጨ በዓመቱ ራሱን ማጥፋቱን ከሳምንት በፊት በሕዝብ ትራንስፖርት ከአራት ኪሎ ወደ መገናኛ ስጓዝ በሬዲዮ ሲነገር ሰምቻለሁ:: ታዋቂነትን ለማግኘት የሞከረውን ጋዜጠኛ ድርጊት ብዙዎቻችን የምንፈጽመውን የሚወክል ነው:: ብዙዎቻችን በሰው ቍስል ለመታወቅ እንጂ የሰዎችን ቍስል ለማጠብና ችግራቸውን ከሥሩ ነቅሎ ለመጣል አስበን አንሠራም:: ጥፋተኝነት ተሰምቶት በጸጸት ራሱን ሲወቅስ ከርሞ ራሱን እንዳጠፋው ጋዜጠኛ የዕድሜ ልክ ጸጸት እንዳናተርፍ መጠንቀቅ በዚህ ዘመን ለችግር የተጋለጡ ወገኖችን ለመርዳት የምናስብ ሁሉ የምንፈጽመው ሊሆን ይገባል:: ብዙዎቹ የሰብአዊ ርዳታ ድርጅቶች ድርጊት በተጎጂዎች ቍስል እንጨት የመስደድ ያህል በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ለመከራ የተጋለጡትን ስንረዳ

ከገንዘብ በላይ የሚያስፈልጋቸው ነገር መኖሩን በመረዳት ሊሆን ይገባል።
ለችግር በተጋለጡ እና ከመኖሪያ ቤታቸው በተፈናቀሉ ሰዎች ጉዳት መነገድ ከሰብአዊ ክብር መውረድ በመሆኑ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እንደ ፎቶ ግራፍ አንሽው ሰው ታዋቂነትን ከመሻት ባሻገር ሰብአዊነትን የሚፈታተን ጥያቄ ቀርቦብን ወደ ልቡናችን እንድንመለስ የሚያደርግ ነገር ገጥሞን በጸጸት ረመጥ ስንለበለብ እንዳንኖር ከመታወቁ እና ከሁሉ ነገር በፊት መቅደም የሚኖርበት የተጎጂዎችን ሰብአዊ ክብር በጠበቀ መልኩ መደገፍ ነው። ይህን ለማድረግ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅባት ኃላፊነት ከባድ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ሐኪሞች ከሚያደርጉት የበለጠ እንዲያውም ለንጽጽር የማይቀርብ ነው። ሐኪሞች ወገን፣ ጠላት ሳይለዩ በጦርነት የተጎዱትን ሁሉ አክመው እንደሚያድኑ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም የተጎዱትን ሁሉ ለመርዳት ኃላፊነት አለባት። አባቶቻችን በየሐኪም ቤቱ እየሔዱ የሚጠይቁትም ወገን ለይተው፣ ቋንቋውን ከግምት አስገብተው ሳይሆን ሰው መሆኑን አይተው መሆኑን እያሳዩን በመሆኑ ይህ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ማኅበረ ቅዱሳን የወገኖቻችን ችግር ችግራችን ነው ብለው የሚያምኑ ወገኖቻችንን በማስተባበር ችግረኞችን ለመታደግ የሚውል ገንዘብ እና ለችግረኞች የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ የሚሰበስበው ለችግር የተጋለጡት ወገኖች የቤተ ክርስቲያን አባል፣ የክርስቶስ አካል መሆናቸውን አውቆ ከገንዘቡ እና ከቍሳቁሱ በላይ የሆነ ድጋፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተረድቶ ነው።

## ሰብአዊነትን ማስቀደም

ለሰው መልካም ከማድረግ ማዘን ይቀድማል። ርኅራኄን የቋንቋና የባህል አጥር አያግደውም። መጋቢት ወር 2011ዓ.ም የኢትዮጵያ አየር መንገድ ንብረት የነበረ አውሮፕላን ደብረ ዘይት አካባቢ ኤጀሬ ከሚባል ቦታ ተከስክሶ ነበር። በወቅቱ የተፈጸመው ድርጊት እንቅልፍ የነሣት አንዲት የአካባቢው ክርስቲያን በየቀኑ አደጋው ወደ ደረሰበት ቦታ እየሔደች ኀዘኗን ትገልጥ ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን በአደጋው የሞቱትን ወገኖቻችንን ሃይማኖት ማጣራት ሳያስፈልጋት ከሣልስት እስከ ዓመታት አስቈርባለች። የዚያች ሴት ድርጊት ሰብአዊነት ተሰምቶን ችግር የገጠማቸውን ለመርዳት ለምንነሣ ሁሉ አብነት የሚሆን ነው። ርዳታችን ከቅድመ ሁኔታ የራቀ፣ ሰው መሆናቸውን ብቻ ከግንዛቤ ያስገባ መሆን የሚገባ መሆኑን የዚች ሴት ድርጊት ያስገነዝበናል።

## በቀደምቶቻችን የደረሰውን ማስታወስ

በዚህ ዘመን ደጋግመን ልናነበው የሚገባን አምላካዊ ቃል“እንግዲህ ምን እላለሁ? ስለ ጌዴዎን፣ ስለ ባርቅ፣ ስለ ሶምሶን፣ ስለ ዮፍታሔ፣ ስለ ዳዊት፣ ስለ ሳሙኤልና ስለ ሌሎች ነቢያት እነግራችሁ ዘንድ ጊዜየ አጭር ነውና። እነርሱ በእምነት ተጋደሉ፤ ነገሥታትን ድል ነሡ፤ ጽድቅን አደረጉ፤ ተስፋቸውን አገኙ፤ የአናብስትን አፍ ዘጉ፤ የእሳትን ኃይል አጠፉ፤ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፤ ከድካማቸው በረቱ፤ በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፤ የባዕድ ጭፍሮችንም አባረሩ። ሴቶችም እንደ ትንሣኤ ቀን ተነሥተውላቸው ሙታኖቻቸውን ተቀበሉ፤ ተፈርዶባቸው የሞቱም አሉ፤ የምትበልጠውን ሕይወት ያገኙ ዘንድ ሊድኑ አልወደዱምና የገረፏቸው፣ የዘበቱባቸውና ያሠሯቸው ወደ ወኅኒ ያስገቧቸው አሉ፤ በመጋዝ የሰነጠቋቸው፣ በድንጋይ የወገሯቸው፣ በሰይፍም ስለት የገደሏቸው አሉ፤ ማቅ ምንጣፍና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤ ተጨነቁ፣ ተቸገሩ፣ መከራ ተቀበሉ፣ ተራቡ፣ ተጠሙም፣ ዓለም የማይገባቸው እነዚህ ናቸው፤ ዱር ለዱርና ተራራ ለተራራ ዋሻ ለዋሻና ፍርኩታ ለፍርኩታም ዞሩ (ዕብ. ፲፩፥ ፴፪-፴፰) የሚለው ነው።

ሐዋርያው ይህን አምላካዊ ቃል የተናገረው በመከራ ጊዜ በእምነት ስለጸኑት በመመስከር ጀማሪዎችን ለማበርታት ነው። ቃሉ ክርስቲያኖችን ምንም ዓይነት መከራ ከዓላማቸው እንደማያናውጣቸው፣ ከአምላካቸውም እንደማይለያቸው የሚያስተምር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ የሚተርከው በጽናታቸው ተደንቆ እንጂ በደረሰባቸው መከራ ተሰቅቆ አይደለም። መከራውን ያልተሰቀቀው የደረሰባቸው አላሳዝነው ብሎ ሳይሆን በእምነታቸው ዓለምን ድል ማድረጋቸው አብሯቸው የነበረ ያህል እየተጋደለ መሆኑን ለመመስከር ነው። የእነዚህ ቅዱሳን ተጋድሎ ቅዱስ ጳውሎስንም በቃል ከመናገር በተግባር ወደ መፈጸም አሸጋግሮት የሮማ ቄሳሮች ያደረሱበትን መከራ የተቀበለው በጸጋ ነው። በቃል የተናገሩትን በተግባር ሲገ ልጡት የሚያስገኘውን ኃሤት ያህል ሰላም የሚያስገኝ ነገር የለምና። ረሃባቸውን ተርቧል፤ መከራቸውን ተካፍሏል። በመከራ ውስጥ ቢሆኑም አለመሸበርን ከቀደምቶቹ በተግባር የተማረው ቅዱስ ጳውሎስ ራሱም የቀዳሚዎችን አሠረ ፍኖት ተከትሎ ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማን ነው በማለት ተናግሯል። በዚህ የመከራ ዘመን እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ ታሪኮችን እየሰማን መጽናናት እንጂ ጠ ላት ዲያብሎስ እንዲደሰት በኀዘን ተጨብጠን ውለን ማደር የለብንም።

በእንደዚህ ዓይነት የመከራ ዘመን ምእመናንን ለማጽናናት ከቤተ ክርስቲያን የሚጠበቀውን በቃላት አጠናቆ መጨረስ አይቻልም። በስደት ጊዜ የምትጸልየው ራሱን የቻለ ጸሎት አለ።በአካል የተሰደዱ ወገኖች በመንፈስም እንዳይሰደዱ ጠንክሮ መሥራት በዚህ ዘመን ከምንገኝ ክርስቲያኖች ሁሉ የሚጠበቅ ተግባር ነው። ቤተ ክርስቲያን በቃል ከማስተማር ጀምሮ በሥነ ልቡና እንዳይጎዱ እና ከገጠማቸው ችግር አገግመው ራሳቸውን እንዲረዱ ከማድረግ ጎን ለጎን የሚያስፈልጋቸውን ማሟላትም ይገባታል።

ችግረኞችን ለመደገፍ እና ኃዘን የበረታባቸውን ለማግኘት በአንዱ በኩል አድርጎ ወይም ዋናውን ተዋናይ ቀርቦ ብዙኃንን የመሰብሰብ ሥራ መሥራት ይገባል። ብዙኃንን ለማግኘት የሚቻልበትን ዘዴ አስቦ መሥራት ድካማችን ለፍሬ እንዲበቃ ያደርጋል። ወገኖቻችን የገጠማቸውን ችግር የሚያስረሳ አጽናኝ ተግባር በመፈጸም አካባቢያቸውን እና ንብረታቸውን ከማጣት በተጨማሪ ከእግዚአብሔር እንዳይለዩ መሥራት ከማኅበራት፣ ከሰባክያነ ወንጌል፣ ከግቢ ጉባኤ ማስተባበሪያና በአጠቃላይም ከሁሉም ሰው የሚጠበቅ ኃላፊነት ነው። ክርስቲያኖች

በመተባበር እንዲህ ካደረግን ቤተ ክርስቲያን በመከራ ጊዜ የደረሰችላቸው ወገኖች መከራው ካለፈ በኋላ አይለዩአትም። በየአካባቢው የተከሠተውን ችግር አስቀድሞ መረዳት ወደ መፍትሔ የሚወስደውን መንገድ በግማሽ ይቀንሰዋል። ሊያስከፋቸው እና ሊያስደስታቸው የሚችለውን ጉዳይ ለይቶ ለማወቅ ውጤታማ ተግባር ለመፈጸምም ያግዛል። ሰዎችን ይበልጥ ላለማሳዘን እንድንጠነቀቅ ያደርጋል። ቤተ ክርስቲያን አታስፈልገኝም የሚል ነውጠኛ ቢኖር እንዴት በመንፈሳዊ ጥበብ ማምጣት እንደሚቻል ለማሰብ ዕድል ይሰጣል።

## ከችግር መውጫ መንገዶች

በአሁኑ ጊዜ በመከራ የተጋለጡ ሰዎችን መርዳት እንደሚገባ የሚታወቅ ቢሆንም ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ እና ከሌሎች እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ዋናው ተግባር ሊሆን ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን የምትረዳው ሃይማኖታቸውን ጠይቃ፣ የሚናገሩትን ቋንቋ ከግምት አስገብታ አይደለም። እንዲያውም ብርሃንነቷ ለአሕዛብ ይገለጥ ዘንድ አስቀድማ የምትረዳው ሌሎችን ነው። በ1983 ዓ.ም በተደረገው የመንግሥት ለውጥ ከብላቴ ወደ ኬንያ ገብተው የነበሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ርዳታ ሲቀርብላቸው ኦርቶዶክሳውያኑ የራሳቸውንም ድርሻ ለሌሎች ይለቁ ነበር። ይህም ብዙዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ ምክንያት ሆኗል። ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነት መልካም ተግባር መፈጸሟ የማያውቋት ለካ ቤተ ክርስቲያን ማለት እንዲህ ናትን? ክርስቲያኖች የሚባሉት እንዲህ ዓይነት በጎ ምግባር አላቸውን በማለት እንዲደነቁ፣ የማያውቁትን ሕይወት እና በጎ ምግባር ዓይተው እንዲማሩ ያደርጋል። በየዘመናቱ የተነሡ ክርስቲያኖች ኢአማንያንን አሳምነው ወደ ክርስትና ሲያስገቡ የኖሩት በእንደዚህ ዓይነት ተግባር ነው።

በአንድ ወቅት ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ የሚባሉ  በሀገረ ግብፅ የእንዴናው ሀገረ ስብከት ኤጲስ ቆጶስ ነበሩ። ጳጳሱ የወንጌል ገበሬ ስለነበሩ በሀገረ ስብከታቸው እየዞሩ ወንጌለ መንግሥትን ለክርስቲያኖችም፣ለአሕዛብም ያስተምሩ ነበር። ቅዱሱ አባት ዞረው ወንጌልን ማስተማራቸው የጠቅላይ ግዛቱን ገዥ አበሳጨው። ስለተበሳጨም በክርስቶስ ማመንህን፣ ከቦታ ቦታ እየሔድክ ወንጌልን ማስተማርህን ተው በማለት አቋማቸውን የሚለውጡ መስሎት በመጀመሪያ በማባበል፣ ቀጥሎ ደግሞ በማስፈራራት ሞከረ። አባ ጢሞቴዎስ ግን ድሆችን ከመደገፍ፣ ከማስተማር እና ከማጽናናት፣ አሕዛብን ከማስተማር ባለመቆጠባቸው ገዥው ይዞ አሰራቸው። ማሰር ብቻ ሳይሆን ጥኑ ስቃይ አደረሰባቸው። መከራ ሲበዛ ጸጋ እግዚአብሔር ይበዛልና ቅዱሱ አባት በመከራ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ብዙ ምሥጢራት ተገለጡላቸው።

መከራን በደስታ መቀየር የባሕርይ ገንዘቡ የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን በዋሉበት አላሳድር፣ ካደሩበትም አላውል ይል የነበረውን ዲዮቅልጥያኖስን ዐሳልፎ ደጉን ንጉሥ ቈስጠንጢኖስን በሀገረ ሮሜ አነገሠው። ንጉሥ ቈስጠንጢኖስም የታሰሩት ክርስቲያኖች እንዲፈቱ፣ የተሰደዱት እንዲመለሱ፣ የተዘጉ አብያተ ክርስቲያን እንዲከፈቱ በማለት ዲዮቅልጥኖስ በዐዋጅ የዘጋውን በዐዋጅ ከፈተው። በዐዋጁ መሠረትም አባ ጢሞቴዎስም ከእስር ተፈትተው ወደ ሀገረ ስብከታቸው ወደ እንዴናው ተመለሱ። እንደደረሱም የሀገረ ስብከታቸውን መነኰሳት፣ ካህናት፣ ዲያቆናት እና ምእመናን ሰብስበው ለአገረ ገዥው እንጸልይለት አሏቸው። ሰዎች ወደ ቅዱሱ አባት ቀርበው ላሰቃየህ ሰው ለምን እንጸልይለት ትላለህ? ብለው በጠየቋቸው ጊዜ መልሳቸው እሱ ባያሰቃየኝ ኖሮ እግዚአብሔርን አላገኘውም ነበር። በመሰቃየቴ እግዚአብሔር የተደበቁ ምስጢራትን ገልጦልኛል በማለት መለሱላቸው።

**ሁል ጊዜ ጨለማን መውቀስ በሕይወት ላይ ለውጥ እንደማያመጣ ተረድቶ የሚገባው ጨለማው እንዲወገድ መሥራት ነው። ክርስቲያኖች ካለ መከራ ኖረን አናውቅም።**

ክርስቲያኖች በቅዱሱ አባት መሪነት በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ከማታ እስከ ጧት ሲጸልዩ እንደሚያድሩ የሚያውቁ ሰዎች ወደ አገረ ገዥው ሔደው አባ ጢሞቴዎስ እየጸለዩለት መሆኑን ነገሩት። የሰዎችን ቃል የሰማው አገረ ገዥ "ለካ የክርስቲያኖች ሃይማኖት እንዲህ ነውን?" በማለት በጣም ተደነቀ። ወደ አባ ጢሞቴዎስ ልኮ ካስወሰደው በኋላ ስለሃይማኖቱ ጠየቀው። ቅዱሱ አባት በየዋህነት ሲያጫውተው አገረ ገዥው ልቡ ተነካ። "እኔ እኮ ያን ያህል ስቃይ ስለአጸናሁብህ  የምትረግመኝ እንጂ የምትጸልይልኝ አልመሰለኝም ነበር" አለው። አባ ጢሞቴዎስም ክርስቲያኖች ማንንም አይረግሙም በማለት መለሱለት። ገዥውም ስለሃይማኖትህ አስተምረኝ በማለቱም አስተምረው አጠመቁት። ከዚያም አገረ ገዥው የነበረውን ገንዘብ ለድሆች ሰጥቶ በአባ ጢሞቴዎስ ሥር መኖር መጀመሩን ኅዳር ፲፫

ቀን የሚነበበው ስንክሳር ይተርካል (ስንክሳር ከመስከረም እስከ የካቲት፣ ፲፱፺፫ዓ.ም÷፪፻፺፰-፪፻፺፱):: በየዘመናቱ ክርስቲያኖች ሲፈጽሙት የኖሩት ተግባር እንዲህ ዓይነት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር የተማሩትም ከቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ለኢአማንያን ጭምር የምትጸልየው እንደ አገረ ገዥው ዓይነት ክፉ ሰዎች አምነው እንዲጠመቁ፣ አልታያቸው ብሎ የነበረው ብርሃኗ እንዲገለጥላቸው ነው፡፡

በዚህ ዘመን የምንገኝ ክርስቲያኖች መፈጸም የሚኖርብንም እንዲህ ዓይነት ምግባር ነው፡፡ ለሚገድሉንም ልንጸልይላቸው እንደሚገባ ቅዱሱን አባት አብነት ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ከአራዊት የከፋ ጨካኝ የነበሩትን ሰዎች በጸሎትም ይሁን በሌላ ምክንያት ወደ ልባቸው እንዲመለሱ አድርጎ ከመከራ አድራሽነት ወደ መከራ ተቀባይነት የሚቀይራቸው የክርስቲያኖች ጽንዓት ነው፡፡ ከዚህ ድርጊት የምንማረው ሰዎች ለመከራ ሲጋለጡ ሒዱ እሳት ሙቁና ጥገቡ ማለት ሳይሆን የሚያስፈልጋቸውን ማሟላትም የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ረሐባቸውን በምግብ፣ ኀዘናቸውን በምክር ማስረሳት በዚህ ዘመን ከምንገኝ ክርስቲያኖች ሁሉ ይጠበቃል፡፡

መከራ የገጠማቸውን ሰዎች ሁሉ እንዴት መርዳት እንደሚገባ አስተማሪ የሆነ አንድ ታሪክ መጨመር አስፈላጊ ነው፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ በ፲፱፷፰ ዓ.ም ታኅሣሥ ወር ታጣቂዎች በከፈቱባቸው ተኩስ ተመትተው ሐኪም ቤት ገብተው በነበረበት ወቅት አካላቸው መራመድ ከማይችልበት ደረጃ መድረሱን ተረድተው ተስፋ እስከ መቁረጥ ደርሰው ነበር፡፡ መራመድ መቻል አለመቻላቸውን በዘመኑ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሐኪም የነበሩትን ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስን ሲጠይቋቸው በቶሎ መልስ አልሰጧቸውም ነበር፡፡
እርሳቸውም ቆሜ መሔድ ካልቻልኩ በሕይወት መቆየት አልፈልግም በማለት ሲናገሩ የሰሙት ፕሮፌሰር አሥራት የምትኖረው ወታደር ለመሆን ነው እንዴ? እጅ አለህ ትጽፋለህ፣ አፍህ ደኅና ነው ታስተምራለህ፣ አእምሮህ ደኅና ነው አስበህ ትሠራለህ በማለት ከመከሯቸው በኋላ እንግሊዝ አገር ሔደው መታከም እንዳለባቸው አሳብ ያቀርቡላቸዋል፡፡ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌም አሳቡን በቶሎ ይቀበሉታል፡፡ ጌታቸው አሳቡን የተቀመሉት ቶሎ ድነው ቄመው ለመሔድ ሲሆን ፕሮፌሰር አሥራት ግን አሳቡን ያቀረቡበት ምክንያት ጌታቸው ባይድኑ እንኳ ከእርሳቸው የበለጠ የተጎዱትን አይተው ራሳቸውን ያጽናናሉ በማለት ነበር፡፡ አሳባቸው ተሳክቶ ጌታቸው እንግሊዝ አገር ሔደው ከተባለው ሐኪም ቤት ሲገቡ በ2ኛው የዓለም ጦርነት ከፍተኛ ጉዳት የደረሰባቸውን ወታደሮች ዓይተው በእነርሱ ዓይን የራሳቸውን ጉዳት ሲመለከቱት "አካለ ስንኩል መሆኔን ረስቼው ልረዳቸው እጄን መዘርጋት ቃጣኝ፡፡ የተደረገልኝ ዋናው ሕክምና እነርሱን ዓይቼ ራሴን
እንዳውቅ መደረጉ ነው" ብለዋል፡፡ ጌታቸው ኃይሌ ቄመው መሔድ ባይችሉም ከደረሰባቸው አካላዊምሪ ሥነ ልቡናዊም ስብራት ወጥተው በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የተመለከቱ ጥናታዊ ጽሑፎችን አበርክተዋል፡፡ ለካ አሥራት ወደዚህ ቦታ እንድመጣ ያደረገው እንድድን ብቻ ሳይሆን ከእነዚህ ቊስለኞች እንድማርም ጭምር ነው በማለት ራሳቸውን ያጽናኑት" (አንድ አፍታ ላውጋችሁ፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም÷ ፪፻፵፮-፪፻፷፩) በዘመናችን በተፈጠረው ጦርነት መከራ ለገጠማቸው ወገኖች አርአያ የሚሆን ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ለችግር የተጋለጡትን ወገኖቻችንን ስንረዳም የረጅዎችን እጅ ዓይተው እንዲያድሩ ብቻ ሳይሆን ራሳቸውን እንዲችሉ፣ የገጠማቸውን ችግር ረስተው አዲስ ሰው እንዲሆኑ የመፍትሔውን ቊልፍ በማሳየት ጭምር ሊሆን ይገባል፡፡ ሁል ጊዜ ጨለማን መውቀስ በሕይወት ላይ ለውጥ እንደማያመጣ ተረድቶ የሚገባው ጨለማው እንዲወገድ መሥራት ነው፡፡ ክርስቲያኖች ካለ መከራ ኖረን አናውቅም፡፡ መከራው የሚያስገኘውን መንፈሳዊ ጥቅም በመረዳት እና የሚጠብቀን ሰማያዊ በረከት እንዳለ በማመን መጽናናት ይኖርብናል፡፡ በአገር ላይ መከራ ሲመጣ ቅርሶች እንዳይወድሙ፣ ክርስቲያኖች ሞተው እንዳያልቁ፣ ንዋየ ቅድሳት እንዳይጠፉ በዘመኑ ሰማዕታት በሮም የነበሩ ክርስቲያኖች በካታኮምብ(በዋሻ) ያሳለፉትን ሕይወት እና መንፈሳዊ ፈሊጥ መከተል በስደት ላይ ከሚገኙም በስደት ላይ ያሉትን ከምንረዳውም የሚጠበቅ ተግባር ነው፡፡

## ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው ከመመለሳቸው በፊት መሠራት የሚገባው

በጦርነቱ ምክንያት በየቦታው ለችግር የተጋለጡ ተማሪዎችን መታደግ የሚገባን አቅማቸውን እና የየአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በቁሳዊ ነገርም በመንፈስም ለመደገፍ መሥራት ቀዳሚው ተግባር ነው፡፡ ጦርነት ቤተሰብን መበተኑ፣ ማፈናቀሉ፣ ሀብት ንብረትን ማውደሙ፣ የማይረሳ ጠባሳ ጥሎ ማለፉ የታወቀ ነው፡፡ ጦርነት በተከተሠባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ታዳጊዎች ወደ ትምህርት ቤት የሚመጡት ይህን ችግር እንደያዙ በመሆኑ ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት አእምሮዋቸውን ነፃ የሚያደርግ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ችግር ያለባቸውን ወገኖች በፍቅር ስቦ ቤተ ክርስቲያን የምትፈጽመው ነገር በአእምሯቸው ተቀርጾ እንዲቀር መሥራት ለነገ የማይባል መንፈሳዊ ኃላፊነታችን ነው፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ ትውልድን ለመታደግ ኃላፊነት ለአእምሮ ሰላምን ከሚያስገኙ ተግባሮች ቀዳሚው ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያንን ተልእኮ ይዘው ለአገልግሎት የሚሰማሩ መምህራን ችግሩን መለየት ብቻ ሳይሆን ችግሩ ሊወገድ የሚችልበትን ማሰብ፣ ከአባቶች ጋር መመካከር፣ ስምምነት ላይ የተደረሰበትን ጉዳይ ተግባራዊ ለማድረግ አለመዘግየት ያስፈልጋል፡፡

በአንድ አካባቢ የተከሠተ ችግር በሌላ ቦታ ከተከሠተ ችግር ስለሚለያይና ግብረ መልሱ ላይገናኝ ስለሚችል አገልግሎቱን እንደ ሁኔታው ማከናወን ይገባል፡፡ ችግሩን መምህራን ብቻ

ወደ ገጽ ፳፰ ዞሯል

# ናሁ ሠናይ ወናሁ አዳም ሶበ ይሄልዉ አኃው ኅቡረ

(መዝ. ፻፴፪፥፩)

ክፍለ ማርያም

ነቢየ እግዚአብሔር ዳዊት ቃሉን የተናገረው ስለትሩፋን ሲሆን ፍጻሜው ግን ስለምእመናን ነው። እስራኤል በፋርስ በባቢሎን ተማርከው እንደሚሔዱ አስቀድሞ ተገልጾለት የተናገረው ቃል ነው። በመሆኑም "ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ መልካም መሆኑን መናገሩ ነው። እነሆም ያማረ ነው" በማለት ሲናገር በፋርስ ባቢሎን የነበሩ እስራኤላውያን ከምርኮ ተመልሰው በኢየሩሳሌም ካሉት እስራኤል ጋር በአንድነት ቢቀመጡ መልካም መሆኑን መናገሩ ነው። አንድነት መልካም ነው፤ እጅግም አስፈላጊ ነው። ስለሆነም ቤተ ክርስቲያን በአንድነት መኖርን ለዘመናት ስታስተምረው ኑራለች፤ ዛሬም ታስተምረዋለች፤ ወደ ፊትም ስታስተምር ትኖራለች። ይሁን እንጂ በዚህም ዓለም በወዲያኛውም ዓለም በአንድነት መኖር የሚችሉ፣ በአንድነት መኖር የሚገባቸውም አካላት እንዳሉ ሁሉ አንድ መሆን የማይችሉ አካላትም አሉ። አንድ ስለሚሆኑት ከመናገር አስቀድሞ አንድ የማይሆኑትንና የሚሆኑትን መለየት ያስፈልጋል።

**አንድ የማይሆኑ ነገሮች፡-** ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አንድ ሊሆኑ የማይችሉትን ነገሮች አንድ ማድረግ እንደሌለብን "ተጠራጣሪዎች አትሁኑ፤ ወደማያምኑ ሰዎች አንድነትም አትሒዱ፤ ጽድቅን ከኃጢአት ጋር አንድ የሚያደርጋት ማን ነው? ብርሃንንስ ከጨለማ ጋር የሚቀላቅል ማን ነው? ክርስቶስን ከቤልሆር ጋር አንድ የሚያደርገው ማን ነው? ወይስ ምእመናንን ከመናፍቃን ጋር አንድ ወገን የሚያደርጋቸው ማን ነው? የእግዚአብሔርን ታቦትስ በጣዖት ቤት ውስጥ የሚያኖር ማን ነው? የሕያው እግዚአብሔር ማደሪያዎች እኛ አይደለንምን? እግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተናገረ 'እኔ በእነርሱ አድራለሁ፤ በመካከላችውም እኖራለሁ፤ አምላካቸውም እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ሕዝቤ ይሆኑኛል። ስለዚህ ከመካከላቸው ተለይታችሁ ውጡ፤ ከእነርሱም ተለዩ፤ ወደ ርኵሳን አትቅረቡ፤ እኔ እቀበላችኋለሁ። አባት እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትሆኑኛላችሁ' አለ ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር" (፪ቆሮ. ፮፥፲፬-፲፰) በማለት ማን ከማን ጋር አንድ መሆን እንደሌለበትና ማን ከማን ጋር አንድ መሆን እንዳለበት አስተምሯል። ሐዋርያው አንድ መሆን የማይችሉ ብሎ የጠቀሳቸው የሚከተሉት ናቸው።

**ጽድቅ ከኃጢአት ጋር፡-** ጽድቅና ኃጢአት በአንድ ሰዓት መፈጸም የማይችሉ፣ አንዱ ሲፈጸም ሌላው የሚቀር ስለሆን የሚተባበሩ ነገሮች አይደሉም። ሰው ኃጢአትን መተውና ከኃጢአት ሥራ መለየት ከፈለገ ጽድቅን መሥራት ይኖርበታል። ማንም ሰው እንኳንስ ኃጢአት እየሠራ ጻድቅ ሊሆን ኃጢአት አልሠራም ቢል እንኳን እንዲሠራ የታዘዘውን የጽድቅ ሥራ ካልሠራ ጽድቅን አለማድረጉ ኃጢአት ይሆንበታል። "በጎ ነገር ማድረግን የሚያውቅ የማይሠራትም ኃጢአት ትሆንበታለች" (ያዕ. ፬፥፲፯) ተብሏልና። ጽድቅን ስንሠራ ከኃጢአት እንለያለን፤ ኃጢአትን ስንሠራ ደግሞ ከጽድቅ እንለያለንና ሁለቱ በአንድ እንደማይሔዱ አስረዳን።

ጽድቅን ሲሠሩ የእግዚአብሔር ማደሪያ፣ የቅዱሳን ወዳጅ፣ ኃጢአትን ሲሠሩ ደግሞ የዲያብሎስ ማደሪያ ይሆናሉ። በዚህ ምክንያት ጻድቃንና ኀጥአን አንድ ሊሆኑ አይችሉም። በቅዱስ ወንጌል "በጎቹን በቀኙ፣ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል" (ማቴ. ፳፭፥፴፫) ተብሎ የተነገረው የሚያስገነዝበው ሁለቱ አንድ እንደማይሆኑ ነው። በበግ የተመሰሉት ጻድቃን በቀኝ፣ በፍየል የተመሰሉት ኃጥአን ደግሞ በግራ ይቆማሉ ማለት ነው።"ወደማያምኑ ሰዎች አንድነትም አትሒዱ" የተባልነው የማያምኑትና የሚያምኑት አንድነት ስለሌላቸው ነው።

**ብርሃን ከጨለማ ጋር፡-** "የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃንን ያገኛል እንጂ በጨለማ ውስጥ አይመላለስም" (ዮሐ. ፰፥፲፪) ተብሎ እንደተነገረው በብርሃን የሚመላለስ ጨለማን አያይም፤ በጨለማ ውስጥ የሚመላለስም ብርሃን አያገኝም። "በጨለማ የሔደ ሕዝብ ታላቅ ብርሃን አየ፤ በሞት ጥላና በጨለማ ሀገርም ለነበሩ ብርሃን ወጣላቸው" (ኢሳ. ፱፥፪) ተብሎ የተነገረው ጨለማ በሆነበት ዘመን ብርሃን አለመኖሩን፣ ብርሃን ሲገለጥ ደግሞ ጨለማ መወገዱን ያስገነዝባል። ብርሃን ከጨለማ ጋር አንድነት እንደሌለው ብርሃን የተባለ ክርስቶስን አምነው የሚመላለሱት ጻድቃንና የጨለማ ገዢ የተባለውን ዲያብሎስን የሚያመልኩ ኃጥአን አንድነት የላቸውም። በቅዱስ ወንጌል "ብርሃን ወደ ዓለም መጥቷልና፤ ሰውም ሥራው ክፉ ስለሆነ ከብርሃን ይልቅ ጨለማን መርጧልና። ሥራውም ክፉ የሆነ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፤ ክፉም ስለሆነ ሥራው እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም።" (ዮሐ. ፫፥፲፱-፳) ተብሎ እንደ ተጻፈ ጨለማን ተገን አድርገው ክፉ ሥራን የሚሠሩትና "የዓለም ብርሃን እኔ ነኝ" ያለውን የክርስቶስን ፈቃድ የሚፈጽሙት አንድነት የላቸውም።

**ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር፡-** ክርስቶስ ፈጣሪ

ነው፤ ቤልሆር ደግሞ ፍጡር ነው፤ ፍጡር ብቻም ሳይሆን ፈጣሪውን የካደ፣ ሌላውንም ሲያስክድ የኖረና የሚኖር ነው። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ክርስቶስን ከቤልሆር ጋር አንድ የሚያደርገው ማን ነው" በማለት ያስረዳል (፪ኛ ቆሮ. ፮፥፲፭)።

ነቢይ ኤልያስ ከእግዚአብሔርና ከጣዖት አንዱን መምረጥ አቅቷቸው ይዋልሉ ለነበሩት "እስከ መቼ በሁለት አሳብ ታነክሳላችሁ፤ እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በአልም አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ" (፩ኛ ነገ. ፲፰፥፳፩) በማለት ከሁለቱ አንዱን መከተል እንጂ የሁለቱም ተከታይ መሆን እንደማይችሉ አስረድቷቸዋል።

ክርስቶስ ከቤልሆር ጋር አንድነት እንደሌለው የክርስቶስ ተከታዮች ጻድቃንና የቤልሆር ተከታዮች ኃጥአንም አንድነት የላቸውም። ክርስቶስ ሰውን ለማዳን እንደ ተሰቀለ የክርስቶስ ተከታዮች ጻድቃንም የሰው ልጅ ድኅነትን ያገኝ ዘንድ ያለ ዕረፍት ወደ እግዚአብሔር ይጸልያሉ። ቤልሆር የሰውን ልጅ ድኅነት እንደ ማይፈልግ ሁሉ የቤልሆር ተከታዮች ኃጥአንም የሰውን ድኅነት የማይፈልጉ ክፉ የሆነውን የዲያብሎስን ሥራ ብቻ የሚፈጽሙ ናቸው።

**ታቦት ከጣዖት ጋር፦** ታቦት የእግዚአብሔር፣ ጣዖት ደግሞ የዲያብሎስ ማደሪያ ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ማደሪያና የዲያብሎስን ማደሪያ አንድ ማድረግ አይቻልም፤ አይገባምም። ፍልስጥኤማውያን የቃል ኪዳኑን ታቦት ማርከው በዳጎን ቤት ባስቀመጡት ጊዜ ዳጎን ተሰባብሮ አገኙት። አንድነት አስፈላጊ ቢሆንም አንድ ሊሆኑ የማይችሉ ነገሮችን አንድ ለማድረግ መሞከር ለጥፋት እንጂ ለድኅነት ስለማያበቃ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ጣዖት ከታቦት ጋር አንድነት እንደሌለው በታቦት አስፈላጊነት የሚያምኑና በጣዖት የሚያምኑ አንድነት ሊኖራቸው አይችልም። አንድ ቀን ወደ ታቦት በሌላ ቀን ደግሞ ወደ ጣዖት መሔድም አይቻልም። የእግዚአብሔር ታቦት ባለበት የሚኖሩት እግዚአብሔርን እያመለኩ ይኖራሉ። በጣዖት ቤት የሚኖሩም የሰው እጅ ሥራ የሆነውን ጣዖትን ያመልካሉ። አንድነት ሊፈጠር የሚችለው በጣዖት ቤት የሚኖሩት ከጣዖት ቤት ወጥተው ወደ እግዚአብሔር ሲሔዱ፣ ከአምልኮተ ጣዖት ወጥተው አምልኮተ እግዚአብሔርን ሲከተሉ ነው።

አስቀድመን አንድ ሊሆኑ የማይችሉትን ካየን ቀጥለን ደግሞ ኅብረት ፈጥረው በአንድነት የሚኖሩትን እናቀርባለን። ነቢዩ "ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ እነሆ ያማረ ነው እነሆ መልካም ነው" በማለት የነገረን አንድነት አስፈላጊ መሆኑን ነው። አንድ የሚሆኑ አካላት የሚከተሉት ናቸው።

**በስደት ያሉት ተመልሰው፦** ባሕር ተከፍሎላቸው፣ ጠላት ተገድሎላቸው፣ መና እየወረደላቸው፣ ዐለት ተሰንጥቆላቸው፣ ደመና ተጋርዶላቸው፣ የብርሃን ዓምድ ተተክሎላቸው ከግብፅ ባርነት የወጡ እስራኤላውያን ለሁለት ተከፋፍለው ነበር። መለያየቱ ሳያንሳቸው ጠላት ተነሥቶባቸው በፋርስ በባቢሎን ተማርከው ነበር። ነቢዩ ዳዊት በትንቢት ተገልጾለት መከፋፈል ቀርቶ "የተማረኩትም፣ የተሰደዱትም ተመልሰው፣ በኢየሩሳሌም ካሉት ጋር በአንድነት ቢቀመጡ እነሆ መልካም ነው፤ እነሆም ያማረ ነው" በማለት ተናገረ።

ዛሬም በሀገራችን ጠላት በመራን መንገድና ዲያብሎስ በፈጠረልን የተሳሳተ አስተሳሰብ አንዱ ባለርስት፣ ሌላው መጤና ሰፋሪ በሚል ክፉ መንፈስ በኦርቶዶክስነታቸው ብቻ ከቦታቸው የተፈናቀሉ፣ ሀብት ንብረታቸው የተዘረፈባቸው፣ በባዶ ቦታ ረሓብና ጥም የሚያሰቃያቸው፣ የቀኑ ሐሩር፣ የሌሊቱ ቊር የሚፈራረቅባቸው ብዙዎች ናቸው። እነዚህ ሁሉ ተመልሰው ወደ ቤታቸው ገብተው ለአሳዳጆችም ልቡና ሰጥቷቸው በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው። ጠላት ተነሥቶባቸው የተሰደዱ እንዳሉ ሁሉ በእረኞቻቸው ግዴለሽነትና በራሳቸውም አልታዘዝም ባይነት የጠፉም በርካታ ናቸው። መቶ በጎች ያሉት ባለጸጋ ከመቶ በጎች አንዲቱ ብትጠፋበት ዘጠና ዘጠኙን በምድረ በዳ ትቶ እስኪ ያገኛት ድረስ ወደ ጠፋችው እንደሚሔድ፣ በአገኛትም ጊዜ ደስ ብሎት በትክሻው ተሸክሞ ወደ ቤቱ እንደሚገባ ወዳጆቹንና ጎረቤቶቹን ጠርቶ የጠፋችውን በጌን አግኝቻታለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ እንደሚላቸው፣ እንዲሁም አሥር ድሪም ያላት ሴት ብትኖር አንዲቱ ብትጠፋባት መብራት አብርታ በቤቷ ያለውን ሁሉ እየፈነቀለች እስክታገኛት ድረስ ተግታ እንደምትፈልግ ያገኘቻት እንደሆነም ወዳጆቿንና ጎረቤቶቿን ጠርታ የጠፋችውን ድሪሜን አግኝቻታለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ እንዳለቻቸው ተጽፏል። የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ቤት ሲመለስ አባቱ ጎረቤቱን ጠርቶ "ፍሪዳ አዘጋጁ፤ ልብሱን ለውጡለት፤ ጫማ አጫሙት፤ ይህ ልጄ ሞቶ ነበር፤ አሁን ግን ሕያው ሆኗልና፤ ጠፍቶም ተገኝቷልና ደስ ይበለን፤ ሐሴትም እናድርግ" በማለት እንዳስተማረው ንስሓ በሚገባ አንድ ኃጢአተኛ በሰማይ መላእክት ዘንድ ታላቅ ደስታ እንደሚሆን አስረድቷል(ሉቃ. ፲፭፥፩-፴፪)።

**ከሃይማኖት ውጪ የሆኑት አምነው፦** ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክረስቶስ ከሰማየ ሰማያት የወረደው፣ ከድንግል ማርያም የተወለደው፣ በተዋሐደው ሥጋ የተሰደደው፣ የተራበው፣ የተጠማው፣ የተሰቀለው፣ የሞተው መለያየትን አጥፍቶ አንድ ሊያደርገን ነው። የተከፈለለትን የደም ዋጋና የድኅነት ምሥጢር ተረድቶ አንድነትን፣ ኅብረትን፣ ሰላምን፣ ተዋሕዶን በምትሰብከው በአንዲት ቤተ ክርስቲያን በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው፤ እጅግም ያማረ ነው። "ያዕቆብ በላ፤ ጠገበም፤ የተወደደውን ጥጋብ አቀናጣው፤ ሰባ፤ ወፈረ፤ ሰፋ፣ የፈጠረውን እግዚአብሔርን ተወ፤ ከሕይወቱ ከእግዚአብሔር ራቀ። በዚህ በልዩ ጣዖት አነሣሡኝ፤ በርኵሰታቸውም አስመረሩኝ። ለእግዚአብሔር ያይደለ ለአጋንንት፣ ለማያውቋቸውም አማልክት፣ ድንገት ለተገኙ ለማይሠሩና ለማይጠቅሙ አማልክት፣ አባቶቻቸውም ለማያውቋቸው አማልክት ሠዉ።" (ዘዳ. ፴፪፥፲፭-፲፯) ተብሎ እንደተነገረ የሰው ልጅ በአርአያውና በአምሳሉ የፈጠረውን እግዚአብሔርን ትቶ ጣዖት የሚያመልክ፣

ለፈጣሪ ሳይሆን ለፍጡር የሚሠዋ፣ ሆኗልና ባለማመን የኖረው በሥላሴ አምኖ በቤተ ክርስተያን ቢቀመጥ መልካም ነው።

**አባቶች ከልጆች ጋር ተግባብተው፡-** ሊቀ ነቢያት ሙሴ "የድሮውን ዘመን አስብ፤ የልጅ ልጅንም ዓመታት አስተውል፤ አባትህን ጠይቅ ይነግርህማል፤ ሽማግሌዎችህን ጠይቅ ይተርኩልህማል" (ዘዳ. ፴፪፥፯) በማለት ለእስራኤል ዘሥጋና በቃሉ ለሚያምኑ ሁሉ እንደተናገረው ልጆች የአባቶችን ቃል እየሰሙ፣ አባቶችም ልጆችን ዘመኑን በዋጀ መልኩ፣ እነርሱን በሚመጥን ትክክለኛ አቅጣጫ እየመሩ አባቶች ከልጆች ጋር ተስማምተው በኅብረት ቢቀመጡ የክርስቲያኖች ኅብረት ሌሎችን በፍቅር ይስባል።

ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ በመልእክቱ "እናንተም ከእኛ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ ያየናትንና የሰማናትን እንነግራችኋለን፤ አንድነታችንም ከአብና ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው" (፩ኛ ዮሐ. ፩፥፫) በማለት እንደተናገረው አባቶች ያዩትን፣ ከረጅም የሕይወት ልምድ የቀሰሙትን ተሞክሮና ያወቁትን ዕውቀት ለልጆች እየነገሩ፣ ልጆችም መልካም የሆነውን ከወላጆቻቸውና ከታላላቆቻቸው እየቀሰሙ በኅብረት ቢቀመጡ ክርስትናቸው በማኅበራዊ ሕይወታቸው ይገለጣል። እኅቶች፣ ወንድሞች፣ አባቶች፣ እናቶች በኅብረት፣ በመልካም አንድነት፣ በሰላም እየኖሩ መልካም የሆነውን ተግባር ቢያከናውኑ ከሚገኘው ጥቅም የተወሰኑትን እንመልከት።

**ሀ.ሃይማኖትን ለመጠበቅ፡-** ይህም ከአማኞች ህልውና፣ የቍጥር መብዛትና መቀነስ፣ ዓለማዊ ሕግጋትና ደንቦች የሚፈቅዱላቸው መብት ተጠብቆላቸው ከመኖርና አለመኖር አንጻር የሚታይ እንጂ ሃይማኖት ትጠፋለች ማለት አይደለም። ስለዚህ ርትዕት የሆነችው ሃይማኖት ትጠበቅ ዘንድ በኅብረት ቢቀመጡ መልካም ነው። ክርስትናችን በማኅበራዊ ሕይወታችን እንዲገለጥም ያደርጋል።

**ለ.ሃይማኖትን ለማስፋፋት፡-** ወንጌል ባልተሰበከበት እንዲዳርስ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። በአገልግሎት ጊዜ አንዱ ቢደክም ሌላው እንዲያበረታ፣ የወንድሞች በኅብረት መኖር፣ የአባቶች ከልጆች ጋር ተስማምቶና ተመካክሮ መሥራት፣ መምህራን ከምእመናኑ ጋር ተግባብቶና ተደማምጦ መኖር ወሳኝ ነው። "መንፈስ ቅዱስ አንድ ሲሆን ስጦታው ልዩ ልዩ ነው" (፩ኛቆሮ. ፲፪፥፬) እንደተባለው ሁሉም እንደየጸጋው ሲያገለግል የአማንያን ቍጥር ጨምራል፤ አማኞችም በሰላም ይኖራሉ።

> **ብርሃን ከጨለማ ጋር አንድነት እንደሌለው ብርሃን የተባለ ክርስቶስን አምነው የሚመላለሱት ጻድቃንና የጨለማ ገዢ የተባለውን ዲያብሎስን የሚያመልኩ ኃጥአን አንድነት የላቸውም።**

**ሐ.ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ፡-** ቤተ ክርስቲያን በመስቀል ላይ የተተከለች በመሆኗ የመከራው ጽናት አያሸንፋትም። ፈተናው እስከ ዕለተ ምጽአት ባይለያትም ተሸንፋ ግን አታውቅም። ለዚህ ደግሞ በኅብረት ማገልገል ብቻ ሳይሆን መከራ ሲመጣ መንፈሳዊ መፍትሔ መፈለግም ይገባል። ሐዋርያት በኅብረት ሲኖሩ አኗኗራቸው የማያምኑትን ስቦ እያመጣ ዕለት ዕለት የአማኞች ቍጥር ይጨምር ነበር።"ቃሉንም ተቀብለው ተጠመቁ፤ በዚችም ዕለት ሦስት ሺህ ያህል ሰዎች ተጨመሩ። በሐዋርያት ትምህርትና በአንድነት ማዕድን በመባረክ በጸሎትም ጸንተው ይኖሩ ነበር። ሰው ሁሉ ፈራቸው፤ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ተአምራትና ድንቅ ሥራ ይደረግ ነበር። ያመኑትም ሁሉ በአንድነት ይኖሩ ነበር" (ሐዋ. ፪፥፵፩-፵፯) የተባለው በተግባር ተፈጽሟል።

**መ.የደከመውን ለማጠንከር፡-** ቅዱስ ጳውሎስ "እምነቱ ደካማ የሆነውን ሰው ታገሡት፤ በአሳቡም አትፍረዱ" (ሮሜ ፲፬፥፩) በማለት የተናገረው አንዱ ሌላውን መደገፍ ያለበት መሆኑን ያስገነዝባል። የክርስቲያኖችን መተባበር፣

መረዳዳትና መፈቃቀር የተመለከተ የሌላ እምነት ተከታይ ከሚደረግለት እገዛና ከክርስቲያኖች ሕይወት ተግባራዊ ትምርህርት ያገኛ። "የሚገባስ እኛ ብርቱዎች ደካሞችን በድካማቸው እንድንረዳቸው ነው፤ ለራሳችንም አናድላ። ሁላችንም በእውነትና በመልካም ሥራ ይታነጽ ዘንድ ለባልንጀራችን እናድላ" (ሮሜ ፲፭፥፩) የተባለው ለዚህ ነው።

በኅብረት መኖር መልካም መሆኑ ስለተነገረ ብቻ አንድ ሊሆኑ የማይችሉትን አንድ ማድረግ አይገባም። አንድ ሊሆኑ ከሚችሉት ጋር በኅብረት ኑረን፣ ስጦታችንን ተጠቅመን ብናገለግል ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን አብረናቸው በምንኖረው ጎረቤቶቻችን ላይ በጎ ተጽዕኖ ያሳድራል። የክርስትና ብርሃንነትመ ይገለጥላቸዋል። የተሰደዱት ተመልሰው፣ የተቸገሩት ታግዘው፣ የተለያዩት አንድ ሆነው ለሃይማኖታቸው ጠበቃ መሆን ይገባቸዋል። የተቸገሩትን እንድንረዳና የደከሙትን እንድናበረታ ኅብረት የሚያስፈልገውም ለዚህ ነው። ለተግባራዊነቱም የእግዚአብሔር ቸርነት፣ የድንግል ማርያም ማላጅነት፣ የመላእክት ጥበቃ፣ የቅዱሳን ሁሉ ተራዳኢነት አይለየን። አሜን!!✤

# በሐዋርያት ከተማ ያለች ቤተ ክርስቲያን

**ክፍለ ማርያም**

የተከበራችሁ አንባብያን በዚህ ወር ዕትማችን በደቡብ የሀገራችን ክፍል የሚገኙን መካን ልናስቃኛችሁ ስለወደድን ከአዲስ አበባ ተነሥተን ወደ ምድረ ጉራጌ አመራን:: የጉራጌ ሀገረ ስብከት መንበረ ጵጵስና መቀመጫ ከሆነችው ወልቂጤ ከተማ የሆሣዕናን መንገድ ይዘን ጉዟችንን ቀጠልን:: ጥቂት ከተጓዝን በኋላ የሆሣዕናን መንገድ ትተን ጉዟችንን ቀጥለን ሐዋርያት የምትባለውን ከተማ አገኘን:: የሐዋርያት ከተማ ከወልቂጤ በ፺፪ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ሲሆን ከአዲስ አበባ ፪፻፲ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች:: ሐዋርያት የወረዳ ከተማ ስትሆን በከተማዋ በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስም የታነፀ ቤተ ክርስቲያን ይገኛል:: የቤተ ክርስቲያኑን አመሠራረትና ታሪኩን የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑት ተሰማ ወልደ አማኑኤል ስላጫወቱን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::

## የቤተ ክርስቲያኑ አመሠራረት

ቤተ ክርስቲያኑ አክሊለ ጊዮርጊስ በተባሉ ክርስቲያን በዐፄ ሱስንዮስ ዘመነ መንግሥት ተመሠረተ:: ለመመሥረቱ ምክንያትም የአክሊለ ጊዮርጊስ ባለቤት ዳዊት ደጋሚና ጠንካራ ክርስቲያን ስለነበሩ አሁን በሐዋርያት ስም የሚጠራው ከተማ ከተመሠረተበት ቦታ ፫ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ዕለት ዕለት እየተመላለሱ ያስቀድሱ ነበር:: ሴትዮዋ ከቤታቸው ተነሥተው ቤተ ክርስቲያን ለመድረስ ታላቅ ወንዝ ማቋረጥ ነበረባቸው:: ከዕለታት አንድ ቀን ለማስቀደስ ሲሔዱ ወንዙ ሞልቶ አገኙት::

የአክሊለ ጊዮርጊስ ባለቤት ሕይወታቸውን በሙሉ በጾምና በጸሎት የሚኖሩ ስለነበሩ ጸሎት ሲያደርጉ ወንዙ ለሁለት ተከፈለላቸው:: ተሻግረው ቅዳሴው ሳያልፍባቸው በሰዓቱ ደርሰው አስቀድሰው ተመለሱ:: ለባለቤታቸውም የሆነውን ሁሉ አስረድተው ከወንዙ ወዲህ ቤተ ክርስቲያን ካልሠራህልኝ ወደ ቤተሰቦቼ እንድሔድ ፍቀድልኝ የሚል ጥያቄ አቀረቡላቸው:: በባለቤታቸውም ጥያቄያቸውን ተቀብለው ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ፈቃደኛ ሆኑ:: ሴቲቱም የሚሠራው ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት ስም እንዲሰየምላቸው ባላቸውን አሳሰቡ፤ ጥያቄውም ባለቤታቸው ተቀባይነት አገኘ::

አክሊለ ጊዮርጊስ በተጠየቁት መሠረት ቤተ ክርስቲያን ለመሥራት ሲዘጋጁ በዚያ ዘመን ጽላት የሚገኘው ጎንደር ስለነበር ወደዚያ ተጓዙ:: እንደ አሁኑ ትራንስፖርት ስላልነበር፣ ጉዞው በእግር ወይም በከብት ጀርባ ስለሚሆን ቅዳሜ፣ እሑድ እና በታላላቅ በዓላት ቀን እንዲሁም ሲደክማቸው አንድም፣ ሁለትም ቀን ዕያረፉ ይጓዙ ስለነበር ለመሔድ ብቻ ስድስት ወር ፈጀባቸው:: ከቦታው ደርሰው ከጳጳሱ ታቦት፣ አገልጋይ አንድ ካህንና አንድ ዲያቆን ተቀብለው ተመልሰው ስድስት ወር ፈጅቶባቸው በዓመታቸው ከቤታቸው ገቡ:: እንደተመለሱም መቃኞ ሠርተው ያመጡትን ታቦት አስገቡ::



የሐዋርያ ቤተ ክርስቲያን

## ከምሥረታው ጀምሮ እስከ አሁን የነበረው ሁኔታ

አክሊለ ጊዮርጊስን በአካባቢው የሚያግዛቸው ሰው ባይኖርም ለግንባታ የሚሆን ድንጋይ፣ እንጨት፣ ሣር፣ ውኃ በቅርብ ይገኝ ስለነበር ልጆቻቸውንና ለአገልግሎት ያመጧቸውን ዲያቆንና ካህን ይዘው ሕንፃውን አጠናቀው ታቦቱን አስገቡ:: ልጆቻቸው ሲያድጉ ወደ ምድረ ከብድ፣ ወደ ደጋ፣ ወደ ምሁር ኢየሱስ ገዳም ሲሔዱ ታላቁ ልጃቸው ከቦታው በመቅረት ቤተ ክርስቲያኑ እንዲጠናከር፣ አገልግሎቱም እንዲስፋፋ አድርጓል:: እስከ ዛሬም ይህ ቦታና ቤተ ክርስቲያኑም የአንጋፋው ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይጠራል:: ከአክሊለ ጊዮርጊስ ጀምሮ ትውልዱ ሲቈጠር በአሁኑ ጊዜ አሥራ አምስተኛ ደርሷል:: በ፲፰፻፸ዎቹ አካባቢ ሐሰን እንጃሞ በሚባል ሙስሊም ጦርነት ተነሥቶ በርካታ ክርስቲያኖች ከክርስትና ወደ እስልምና ሔዱ፤ ሃይማኖታችንን አንለውጥም ያሉትም ሰማዕትነት ተቀበሉ:: ይህን ታሪክ ወርቁ ንዳ የተባሉ የታሪክ ምሁር "ጀብዱ የጉራጌ ባህልና ታሪክ" በተሰኘ መጽሐፋቸው "ሐሰን እንጃሞ በሳሊያ ለሜቻ የተመራ ኃይል ወደ ቆላው ምሁር በመላክ ክርስቲያኖችን በሁለት አቅጣጫዎች እንዲያጠቋቸው አድርጎ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ላይ ነበር የእስላሞቹ ጦር ከእዣ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ዘምቶ የከሬብን ወንዝ ከተሻገረ በኋላ ወደ ላይ እስከ የምናን ድረስ በመገስገስ ከአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከክርስቲያኖች ጋር የተገናኘው:: እዚያ ቦታ ላይ ውጊያው በጠዋት ተጀምሮ ለብዙ ሰዓታት እንደ

ቆየ ይነገራል:: በመጨረሻም ክርስቲያኖቹ ከእስላሞቹ በቊጥር ስለሚያንሱ ተሸነፉ፤ አብዛኞቹም አለቁ፤ የተረፉት የምሁር ክርስቲያኖች ወደ ከሬብ ጫካ ገብተው ተሸሸጉ:: እስላሞቹ ያገኙትን ክርስቲያን መግደል፣ በአካባቢው የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ማቃጠል፣ የክርስቲያኖችን ቤትም መዝረፍና መደምሰስ ሥራየ ብለው ተያይዘውት ነበር" (ወርቁ፣ ፲፱፻፹፫፣ ፻፲፮-፻፲፯) በማለት ገልጠውታል::

ወርቁ ንዳ አክለውም "ምሁር ውስጥ ይገኙ ከነበሩት አርባ አራት አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዱ ብቻ ሲቀር ሁሉም በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች በእሳት ወድመዋል:: የተረፈው ቤተ ክርስቲያን ሀገረ ማርያም ሲሆን የዳነውም በመጀመሪያ ሊያቃጥሉት እሳት ለኩሰውበት አልያያዝ ሲል ሐሰን እንጃሞ 'ይቺ ጎስጥ ፋጡማ መሪማ ነች' ብሎ አስጥሏት ነው" ( ወርቁ፣ ፲፱፻፹፫፣ ፻፶፮) ይባላል:: በጦርነቱ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበሩ አባ ገብረ ማርያም የሚባሉ አባት ጽላቱን ከቤተ ክርስቲያኑ አውጥተው በከሬብ ጫካ ውስጥ በሚገኝ ዋሻ ደብቀውታል:: ጽላቱን ሲታደጉ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ግን ተቃጥሏል:: ከጦርነቱ በኋላ መቃረቢያ ተሠርቶ ታቦቱን ወደ መንበረ ክብሩ ሊያስገቡ በዝግጅት ላይ ሳሉ አባ ገብረ ማርያም ስላረፉ ከዋሻው ውስጥ ተቀበሩ:: ጽላቱ ግን ወደ አዲሱ ሕንፃ ገባ:: አስቀድሞ ከ፲፮ የማይበልጡ አባ ወራዎች የነበሩ ሲሆን በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም ወደ ወረዳ ስላደገ የአባ ወራዎች ቊጥር ከ፫፻ በላይ ሆኗል::

በአካባቢው የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሰፋፊ ይዞታ ነበራቸው:: ቦታውም ከነገሥታቱ ሲበረከት በአገልግሎት ድርሻ የተከፋፈለ ነበር:: የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ቦታ የቄስ፣ የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የዲያቆን ተባለ:: ከተማው በተመሠረተበት ወቅት የአማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ከተማው በይዞታቸው እንዲመሠረት ፈቃደኛ አልነበሩም:: የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ግን ከተማው እንዲመሠረት ፈቃደኛ ስለሆኑ በቦታው ከተማ ተመሠረተ:: ከተማው ከቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ ላይ ስለተመሠረተ ሐዋርያት ተብሎ መጠራት ጀመረ::

## አሁን ያለበት ነባራዊ ሁኔታ

አንዳንድ ክርስቲያኖች በሐሰን እንጃሞ ጦር ሰልመው የነበረ ቢሆንም ጦርነቱ ካበቃ በኋላ የሰለሙት ንስሓ ገብተው ቄድር እየተጠመቁ ወደ ክርስትና ተመልሰዋል:: በአሁኑ ጊዜ ከ፺፰ በመቶ በላይ የከተማው ነዋሪ ኦርቶዶክስ ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በአንድ ዲያቆንና በአንድ ቄስ ብቻ እየታጠነ ምን አልባትም ከዓመት አንድ ጊዜ ብቻ ከየአካባቢው በሚመጡ አገልጋዮች ይቀደስ የነበረው አሁን ግን ካህናቱም ዲያቆናቱም ተሟልተው አገልግሎት ይሰጣሉ:: በየሳምንቱ እሑድ፣ ወር በገባ በ፳ በጴጥሮስና ጳውሎስ ዕረፍት፣ ወር በገባ በ፲፮ የኪዳነ ምሕረት፣ በ፳፩ የእመቤታችን ይቀደሳል፤ በጾመ ማርያም በ፲፮ቱም ዕለታት ሰዓታቱም፣ ቅዳሴውም አይቋረጥም:: ሁል ጊዜ ኪዳን ይደረሳል:: የዐሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ዓመታዊ በዓላቸው በቅዳሴና በማሕሌት ይከበራል:: ምእመናን እየተደራጁ ዝክር ይዘክራሉ::

## የአብነት ትምህርት

በቦታው የአቋቋም መምህር ስላሉ በርካታ ዲያቆናትን አፍርተዋል፤ እንደ ዲያቆናቱ ባይሆንም አስተምረው ለቅስና መዓርግ ያበቋቸውም አሉ:: ዲያቆናቱ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን የሚማሩትና ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉት የዘመናዊ ትምህርታቸውን እየተማሩ በመሆኑ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የገቡም፣ ተመርቀው በሥራ ላይ የሚገኙም አሉ:: በማገልገል ላይ ያሉ ዲያቆናት ቊጥር ከ፲ በላይ ቢሆንም በዘመናዊ ትምህርት እየቀጠሉ ቦታውን መልቀቃቸው በአገልግሎት የሚተኩትን ቀሳውስት ቊጥር እንዳይጨምር አድርጉታል::

## በቦታው የሚገኘው ጸበል

በጸበሉ ብዙዎች ከልዩ ልዩ በሽታ ይፈወሳሉ:: ጸበሉ የተገለጠው አንድ መምህር ባለቤታቸው ታማ ወደ ዜና ማርቆስ ገዳም እየወሰዱ ሲያስጸብሉ ሌሊት አንዲት ሴት መሪጌታ ተነሡ እንጂ ወደ ጸበሉ እንሒድ በማለት ደጋግማ ትቀሰቅሳቸዋለች:: እርሳቸውም እየተመላለሱ ስለነበር ሁል ጊዜ ወደሚመላለሱበት ጸበል መስሏቸው ከነጋማ እሺ ይላሉ:: ሴትዮዋም ዜና ማርቆስ እኮ አይደለም፤ እዚህ የሐዋርያት ጸበል አለ ትላቸዋለች:: ሲነቁ በሕልማቸው ነው:: ሌሊቱ ተጋምሶ ስለነበር መሪጌታውም ተነሥተው ጸሎታቸውን አድርሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሔዱና የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑትን ካህን መምሬ ገብሬን ያማክሯቸዋል:: ካህኑም "ጊዜው ስላልደረሰ ግልጥ ሆኖ አልወጣም እንጂ ጸበል መኖሩ በአባቶች ይነገር ነበር" ይሏቸዋል:: መሪጌታውም ኪዳን ሲያልቅ ተማሪዎቻቸውን ይዘው በአካባቢው ፍየል የሚጠብቅ እረኛም ጨምረው አለ ወደ ተባለበት አካባቢ ቢሔዱ ዙሪያውን በቁጤማ የተከበበ ረግረግ ቦታ ያገኙና መጥረግ ሲጀምሩ ይፈልቃል:: እርደሳቸውም ጸበል መሆኑን ተረድተው፣ የተገለጸላቸውን ሕልምም አምነው ተመልሰዋል::

ወቅቱ ጾመ ኢየሱስ ስለነበር በዐቢይ ጾም አራተኛው ሳምንት በመፃጕዕ ዕለት ከታላቁ ገዳም ምሁር ኢየሱስ በመሔዱ አባቶች ተባርኮ ክርስቲያኖች መጠመቅ ጀመሩ:: ፴፰ ዓመት የአልጋ ቁራኛ የነበረው መፃጕዕ በተፈወሰበት ዕለት የተባረከው ጸበል ዛሬም በርካታ መፃጕዎችን በመፈወስ ላይ ነው:: ነቢዩ ዳዊት "በልዎ ለእግዚአብሔር ግሩም ግብርከ፤ እግዚአብሔርን ሥራህ ግሩም ነው በሉት" (መዝ. ፷፭፥፫) በማለት እንደ ተናገረው ምእመናን ዓይተው ይረዱ ዘንድ ድንቅ ድንቅ ተአምራት የሚያደርግ ጸበል ፈለቀ:: በጸበሉ ተፈውሰው ምስክርነት ከሰጡት መካከል የመሪጌታው ባለቤት አንዷ ናቸው::

እጅና እግሯ ሰልሎ መንቀሳቀስ ተቸግራ የነበረች አንዲት ሴት በበቅሎ መጥታ ሦስት ቀን ከተጠመቀች በኋላ ተፈውሳ በእግሯ ወደ ቤቷ ተመልሳለች፡፡ ሦስተኛ በወልቂጤም፣ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታልም ተመላልሳ አንችልም ውጪ ሀገር ሔደሽ ታከሚ ብለዋት የነበረች ሴት ውጭ ሀገር ሔጄ መታከም ስለማልችል ሐዋርያት እንዳደረጋችሁ አድርጉኝ ብላ ሰባት ቀን ተጠምቃ ተመልሳ ሔዳ ብትመረመር ነፃ ነሽ ተብላለች፡፡

**የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ግን ከተማው እንዲመሠረት ፈቃደኛ ስለሆኑ በቦታው ከተማ ተመሠረተ፡፡ ከተማው ከቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ ላይ ስለተመሠረተ ሐዋርያት ተብሎ መጠራት ጀመረ፡፡**

## ቅርሳ ቅርስ

ቤተ ክርስቲያኑ ጥንታዊ እንደመሆኑ መጠን በርካታ የብራና መጻሕፍት ይገኙበታል፡፡ የብራና መዝሙረ ዳዊት፣ ተአምረ ማርያም፣ ተአምረ ኢየሱስ፣ ገድለ ሐዋርያት፣ የሁሉም ሐዋርያት መልክ ከሚገኙ መጻሕፍት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ ቤተ ክርስቲያኑን የተከሉት አክሊለ ጊዮርጊስና ሌሎች መኳንንት ያበረከቷቸው የክብር ዕቃዎችም ይገኛሉ፡፡ እንደችግር ከሚጠቀሱት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

## ተምረው ቅስና ተቀብለው በቦታው የሚያገለግሉ ዲያቆናት ቍጥር ማነሱ

ዲያቆናቱ በትምህርታቸው ሲገፉ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመግባት፣ በሥራ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ ስለሚሔዱና በትምህርታቸው የማይገፉትም አዲስ አበባ ሔደው በንግድ ይሰማራሉ እንጂ ትዳር መሥርተው ቅስና በመቀበል በቦታው ለማገልገል ያላቸው ፍላጎት አነስተኛ ነው፡፡ እንዲህ መሆኑም ተተኪ የማፍራት ዕድሉን አናሳ አድርጎታል፡፡ ጥንታውያን ለሆኑ ቅርሶችም ዘመኑን የዋጀ የቅርስ ማስቀመጫ አለመኖር መጻሕፍቱና ሌሎችም ንዋያተ ቅድሳት ለአደጋ የመጋለጥ ዕድላቸው የሰፋ ነው፡፡

የከተማው ነዋሪ ከ፺፰ በመቶ በላይ ኦርቶዶክስ ቢሆንም በሃ ይማኖት የሚያጸነና መንፈሳዊ ትምህርት የሚያስተምራቸው የለም፡፡ ይህም ከጥቂት ዓመታት ወዲህ በከተማው እየተስፋፉ ወደ መጡት ቤተ እምነቶች እንዲሔዱ በር ይከፍታል፡፡ አንዳንድ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን የነበሩ ግለሰቦች በብልጭልጭ ተደልለው ወደ ፕሮቴስታንት መሔዳቸው ሊያነቃን ይገባል፡፡

## መፍትሔው

በትምህርት ላይ የሚገኙት አገልጋዮች ከዲቁና ወደ ቅስና እና መሪጌትነት እንዲያድጉ መሥራት ቢቻል መልካም ነው፡፡ በአንድ ልብ ትምህርታቸውን የሚከታተሉበትን መንገድ አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለተግባራዊነቱም የሚመለከተው አካል ድርሻውን ቢወጣ፣ ኦርቶዶክሳውያንም ብንረባረብ ውጤት እናመጣለን፡፡ ተማሪዎች ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ እንዴት እኖራለሁ የሚለው ሳያሳስባቸው አሳባቸው ሁሉ አገልግሎት ላይ እንዲሆን መደገፍ፣ ከበጎ አድራጊ ምእመናን ጋር በመወያየት ጉባኤ ቤቱ የሚሰፋበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ካህናት ተረጋግተው ኑሯቸውን እንዲመሩ፣ ይልቁንም ዲያቆናት ተግተው እንዲማሩና ወደ ቅስናው መሸጋገር እንዲችሉ ማገዝ ይገባል፡፡ እነርሱን ሊያኖር የሚችል ዘላቂ በጀት ተመድቦላቸው ቋሚ ኑሮ እንዲኖሩ ማድረግ ቢቻል የካህናት እጥረት አያሳስበንም፡፡
ቋሚ የመጻሕፍት መምህር ተመድቦ ተከታታይ ትምህርት እንዲያገኙ የመጻሕፍት ጉባኤ ቤቶችም ተቋቁመው አካባቢውን በወንጌል የሚያደርሱ ሊቃውንት እንዲወጡ ቢደረግ መልካም ነው፡፡ በጊዜያዊና በእንግዳ ትምህርት እየተሳቡ ወደሌላ ቤተ እምነት ከሚሔዱ ቤተ ክርስቲያን ያስተማረቻቸውን ርትዕት ሃይማኖት እንዲያጸኑ ያደርጋል፡፡ ከእናት ከአባቶቻቸው የወረሱትን ክርስቲያናዊ ዕሴትም በዕውቀት አጠንክረው ለቀጣይ ትውልድ የሚያስተላልፉበትን መንገድ ማመቻቸት ቢቻል መልካም ነው፡፡ ለአደጋ የተጋለጡ የብራና መጻሕፍትና ሌሎች ንዋያተ ቅድሳት ሙዚየም ተሠርቶላቸው በአግባቡ ቢቀመጡ፣ ቤተ ክርስቲያኑ በአግባቡ ቢታጠር፣ ጥበቃው ቢጠናከር፣ በልዩ እንክብካቤ ሊቀመጡ የሚገባቸው ንዋያተ ቅድሳትም ትኩረት ቢሰጣቸው በአካባቢው የሚገኙ ሌሎች ቤተ ክርስቲያኖችም አርአያነቱን ሊከተሉ ይችላሉ የሚል እምነት አለን፡፡☩

# የበዓላት ድምቀት ለስብከተ ወንጌል አገልግሎት

**ዲ/ን ማለደ ዋሲሁን**

ቤተ ክርስቲያን በዓላትን የምታከብረው ቱሪዝምን ለማስፋፋት፣ በዩኒስኮ ቅርስነት ለማስመዝገብ፣ ለወጣቶች መዝናኛነት፣ ለባህል ልማት አይደለም። እነዚህ የዚህ ዓለም ጉዳዮች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን በዚህ ዓለም ብትኖርም ከዚህ ዓለም ግን አይደለችም። በዚህ ዓለም የምትኖርበት ዓላማ የታወቀ፣ የተረዳ ነው። ግልጽ የሆነ የመንፈሳዊ አገልግሎት ዓላማ አላት። የምትኖርበት ዓላማ ብቻ ሳይሆን ሥርዓትም አላት። ይህንን የአገልግሎት ዓላማ ለማሳካት ትመረምራለች፤ ትትጋለች። ለዓላማዋ እንቅፋት የሚሆንባትን ሁሉ ዓላማዋን ለማስገንዘብ ታስተምራለች፣ አልሰማት ሲል ታወግዛለች፤ ሞግታለች፤ መሥዋዕትነት ትከፍላለች/መከራ ትቀበላለች/። መሠዋዕትነት ብትከፍልም ታሸንፋለች። ዋናውና በዓዋጅ የተሰጣት አገልግሎት ‹‹ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ››(ማቴ. ፳፰፥፲፱) እና ‹‹መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም፣ በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ›› (የሐዋ.፩፥፰) በማለት በተናገረው ቃሉ አምነው ለተጠመቁ ሁሉ የሰጠው አገልግሎት ነው።

ይህ የስብከተ ወንጌል/የምስክርነት/ አገልግሎት ቅዱስ ጴጥሮስ ቁልቁል የተሰቀለበት፣ ቅዱስ ጳውሎስ የተሰየፈበት፣ ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ የተወገረበት፣ ቅዱስ ያዕቆብ ከቤተ መቅደስ ራስ ቁልቁል የተወረወረበት፣ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ የተጋዘበት፣ ቅዱስ ጊዮርጊስ ዐመድ እስኪሆን በመንኮራኩር የተፈጨበት፣ ቅዱስ አትናቴዎስ በስደት ዘመኑን የፈጀበት፣ ቅዱስ ማርቆስ በምድር ላይ በገመድ የተጎተተበት፣ ብዙ ሰማዕታት በጦር ተወግተው፣ በእሳት ተቃጥለው፣ በአራዊት ተበልተው ደማቸውን እያፈሰሱ መከራ የተቀበሉበት ነው።

ለዚህ አገልግሎት ብዙ ሐዋርያትና አሠረ ፍኖታቸውን የተከተሉት ተላውያነ አበው፣ ሊቃውንት፣ ጳጳሳት እና በየዘመኑ የተነሡ መምህራን እስከ ዓለም ዳርቻ ድረስ ቀን ከሌት በእግር፣ በመርከብ፣ በእንስሳት ጀርባ ተጉዘዋል። በአካል ለማይደርሱት ብዙ መልእክታት ጽፈዋል። ብዙ ዋሻ ቆፍረዋል። ከተርታ ዜጋ እስከ ቤተ መንግሥት ሰዎች ድረስ የልቡናቸውን በር አንኳኩተዋል።
ይህ ሁሉ የሆነው በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የታዘዘውን መተኪያ የሌለውን አገልግሎት ለመፈጸም ነው። ቤተ ክርስቲያን እንድትፈጽመው የተሰጣት አግልግሎት እንዲጠበቅ፣ እንዲደረጅ፣ ጥበብ ያልተለየው እንዲሆን፣ እንዲፈጥን፣ እንዲሳካ የቤተ ክርስቲያን አባቶች ልዩ ልዩ ሕግና ሥርዓት ሠርተዋል። በዚህ አገልግሎት ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን ለሚጨመሩ ነፍሳት መጋቢነትም ሕግና ሥርዓት ተሠርቷል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም በዚህ የአገልግሎት መርሕ መሠረት ቤተ ክርስቲያንን ከጥንት እስከ አሁን ሲያገለግሉና ሲመሩ ቆይተዋል። አባቶቻችን ከሠሯቸው ታላላቅ የአግልግሎት ሥርዓቶች መካከል አንዱ የበዓላት አከባበር ሥርዓት ነው። መነሻቸው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያዘዛቸው፣ በቃሉ የተናገራቸው፣ ፈጽሞ በድርጊት ያሳያቸው እና ቅዱሳን ሐዋርያት ያስተማሩት ትምህርት ነው።

ጌታችን በሰንበት በዓላት ቃሉን ያስተምር ነበር። ቃሉን በማንበብ ያስተምር ነበር። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፲፪ ዓመት ሲሞላው የፈጸመውን እንዳነበብነው የፋሲካን በዓል ሕዝብ በሚሰበሰብበት በኢየሩሳሌም በቤተ መቅደስ በመገኘት ቃሉን ይናገር እንደ ነበር ‹‹የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ፥ እንደ በዓሉ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ፤ ቀኖቹንም ከፈጸሙ በኋላ፥ ሲመለሱ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፤ ዮሴፍም፣ እናቱም አላወቁም ነበር። ከመንገደኞች ጋር የነበረ ስለመሰላቸው የአንድ ቀን መንገድ ሔዱ፥ ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቋቸውም ዘንድ ፈለጉት፤ ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ። ከሦስት ቀንም በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም በመቅደስ አገኙት፤ የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ተገረሙ›› (ሉቃ. ፪፥፵፪) ተብሏል። የበዓል ጊዜ እንደ ሰንበት ሁሉ የአገልግሎቱ ጊዜ ነበር። የተወደደ ሰዓት ነበር። የማዳን ጊዜው ነበር። ከዚያም በኋላ በበዓላት የብዙዎችን ልብ ገዝቶበታል። መጽሐፍም ስለዚህ ሲመሰክር ‹‹ወደ ገሊላም በመጣ ጊዜ፥ የገሊላ ሰዎች ራሳቸው ደግሞ ለበዓል መጥተው ነበርና በበዓል በኢየሩሳሌም ያደረገውን ሁሉ ስላዩ ተቀበሉ›› (ዮሐ.፬፥፵፫) ይላል።

በዓለ ኀምሳም የመንፈስ ቅዱስ የሥራው ጊዜ ነበር። ጌታችን በዐረገ በአሥረኛው ቀን መንፈስ ቅዱስ በሐዋርትና አብረዋቸው በሚያገለግሉ አርድእት ላይ ወርዷል። የሚያገለግሉበትን ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ገልጦላቸዋል። በዕለቱ በተከበረው በዓል በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ሦስት ሺሕ ሰዎች ወደ ክርስቶስ መንግሥት

**በዓላትን በየጊዜው እንዲሰፉና ደምቀው ወደ ቀጣይ ትውልድ እንዲሸጋገሩ የሚያደርጋቸው የበዓላት አከባበራችንን ስናዳብረው ነው፡፡ በዓላትን በሌላ መተካት ወይም መለወጥ ሳይሆን ማዳበር አስፈላጊ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡**

ተቀላቅለዋል (ሐዋ.፪፣ ፵፩)፡፡ ቅዱሳን ሐዋርያት በዓላትን ለስብከተ ወንጌል ተጠቅመዋል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹የሚመጣውን በዓል በኢየሩሳሌም አደርግ ዘንድ ይገባኛል››(የሐዋ.፲፰፥፳፩) ማለቱን እናስተውል፡፡

አባቶቻችን በዓላትን በቤተ ክርስርቲያንም፣ በቤት ውስጥም፣ በአደባባይም ሲያከብሩ ዋነኛ የመንፈሳዊ አገልግሎት መፈጸሚያ እንዲሆኑ እንጂ ሌላ ዓላማ አልነበራቸውም፡፡ በተለይም የጥምቀትም፣ የመስቀል ደመራ በዓልም በአደባባይ የሚከበሩ በዓላት ሁሉን ወገን ማግኘት በሚያስችል ለስብከተ ወንጌል /ለምስክርነት አገልግሎት/ ሰፊ ዕድል የሚሰጡ ስለነበሩ ከጊዜ ጊዜ እያዳበሯቸው ከዘመናችን ደርሰዋል፡፡ የነገዋም ቤተ ክርስቲያን በዓላትን ለስብከተ ወንጌል የመጠቀም ጽኑ ዓላማ የበለጠ ልትቀጥልበት ይገባል፡፡

## በክርስትናችን የማይነቀፉ ማድመቂያ ሥርዓቶችን የበለጠ ማዳበር

በዓላት መከበር በጀመሩባቸው ዘመናት ለማክበር የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ከዘመኑ የአኗኗር ሁኔታ የመነጩ ናቸው፡፡ ሰዎች ለበዓላት ማድመቂያ የሚጠቀሙባቸው ነገሮች ሁሉ በጊዜው ከነበረው ቴክኖሎጂ ዓይነትና ደረጃ የመነጩ ናቸው፡፡ በዓሉን ልናከብር ከተነሣንበት መንፈሳዊ ዓላማ ጋር የማይጋጩ ግብአቶችን በመጠቀም እግዚአብሔርንም ሰውንም የሚያስደስት ተግባር ሲፈጽሙ ኖረዋል፡፡ ባለን ነገር ሁሉ ከልብ ለማገልገል መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ትናንት ያልነበሩ፣ ዛሬ ያሉ የበዓላት ማድመቂያ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ስንጠቀም ወንጌልን ሊያስፋፉ በሚችል መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

ከመቶ ዓመታት በፊት ያልነበረውን ድምፅ ማጉሊያ እና የብዙኃን መገናኛ እንደተጠቀምን በበዓላት ዕለት ልናስተላልፍ ለሚገባን ወንጌል ይጠቅማል ያልነውን ሁሉ መጠቀም ይገባል፡፡ በዓላትን በየጊዜው እንዲሰፉና ደምቀው ወደ ቀጣይ ትውልድ እንዲሸጋገሩ የሚያደርጋቸው የበዓላት አከባበራችንን ስናዳብረው ነው፡፡ በዓላትን በሌላ መተካት ወይም መለወጥ ሳይሆን ማዳበር አስፈላጊ የሚሆነውም ለዚህ ነው፡፡ የማይቀየረው ቃለ እግዚአብሔር እና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ነው፤ ቃለ እግዚአብሔር ግን በይዘት በትርጕም ሳይለወጥ እንዲሰፋም፣ እንዲጠብም ይደረጋል፡፡ እንዲነበብ ወይም እንዲዜም ይደረጋል፡፡ ይህ ሁሉ በዓላት ዘመኑን የዋጁ እንዲሆኑ አድርጎ ለክርስቶስ የሆኑ ነፍሳት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲጨመሩ ምቹ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡

## በበዓላት ወንጌል ጎልቶ እንዲሰማ ማድረግ

የአደባባይ በዓላት የሚከበሩባቸው ዕለታት ጠቃሚ መልእክት የሚተላለፍባቸው እንጂ በማይገቡ ንግግሮችና ባልተደራጀ የበዓል አመራር መባከን የለባቸውም፡፡ የአደባባይ በዓላት ቤተ ክርስቲያን መጥተው የማያውቁ ሰዎች የሚታደሙባቸው በመሆናቸው ክርስቲያናዊ መልእክቶች የሚተላለፉባቸው፣ ወንጌል በስፋት የሚሰበክባቸው ካደረግን በአጋጣሚ የመጣው በዓል አክባሪ አማናዊውን ድኅነት ያገኛል፡፡ ጊዜውን ለምእመናን ትርጕም በማይሰጡ አታካች መርሐ ግብሮች እንዳንጨርሰው መጠንቀቅ ይገባል፡፡ የሚቀርቡ ወረቦች ጎልተው እንዲሰሙ፣ ተነበው ተተርጉመው ምእመናን አብረው በመዘመር እንዲሳተፉባቸው፣ ትርጕሙን አውቀው እንዲመሰጡባቸው የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ፡፡ ትምህርቶች ቤተ ክርስቲያን ሔደው የማያውቁትን ስበው እንዲያመጡ ታስቦባቸው ሊሰጡ ይገባል፡፡ በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰበው ሕዝብ በሚመጥን ደረጃ ማስተማር የሚችሉ የተመረጡ መምህራን እንዲያስተምሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የአባቶች መልእክት የአድማጭን ልቡና እንዲማርክ አስቀድሞ ታስቦበት ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ ሰዓት አጠቃቀማችን የበዓሉን ዓላማ በሚገባ የሚገልጥ መሆን አለበት፡፡

በዐውደ ምሕረት የሚካሔድን ልመናና ጨረታ በማስቀረት አጥቢያዎች የሚፈልጉት ገቢና የተለየ ምክንያት ሲኖር ያልተንዛዛና አጫጭር መልእክቶችን በማስተላለፍ ብቻ ገቢ ለመሰብሰብ ቢሞክሩ የበለጠ ሰዎች ሊሳተፉ ይችላሉ፡፡ ለታዳሚዎች ምን እናድርግላችሁ የሚያስብል አገልግሎት መስጠት ላይ ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ መርሐ ግብር መሪዎች የጎደለውን የሚያቃኑ፣ ትኩረት የተነፈገውን የሚያደምቁ፣ የሕዝቡን ልቡና ከዓውደ ምሕረቱ እንዳይለይ አድርገው የሚያቆዩ ሊሆኑ ይገባል፡፡

የበዓል አከባበር ሥርዓቱን የሚያስረዱ ማስገንዘቢያ መንገዶችም መኖር አለባቸው። የበዓሉን ሥርዓትና እያንዳንዱን ይዞታ ከወንጌል ትምህርት አንጻር እየተረጎሙ ለታዳሚው ማስተማር የበዓሉን የመከበር ዓላማ ያሳካል።

## የሚዲያ አማራጮችን ሁሉ መጠቀም

በዓላቱ አደባባይ ቢከበሩም ሌላ ማዳበሪያ አደባባይ ደግሞ አለ፤ የሚዲያ አደባባይ። ይሄ አደባባይ አሁን በቴክኖሎጂ ተራቆ እያንዳንዱን ሁነት በሰዓቱ ከቦታው ለዓለም ለማዳረስ አስችሏል። እያንዳንዱ ግለሰብም የሚሠራውንና የሚናገረውን የዋለበትን ለወዳጆቹ ማጋራት የሚችልበት ዕድል አለ። ስለዚህ የአደባባይ በዓላት ዘመኑ ባስገኛቸው የቴክኖሎጂ አደባባይም ደምቀው እንዲታዩ መደረግ አለበት። በዓላትን ለሚዲያ አጠቃቀም አመቺ አድርጎ ማዘጋጀት ብልህነት ነው።

ከዚህ ባሻገር ሁሉንም የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጭ ቴክኖሎጂዎች መጠቀም ያስፈልጋል። ሁሉንም የማኅበራዊ ሚዲያ መተግበሪያዎች ሥራ ላይ ማዋልም የበዓሉ አከባበር በአጭር ጊዜ ውስጥ በመላው ዓለም እንዲደርስ ያደርጋል። በዓላት በሚከበሩበት ዕለት ወንጌልን ለመላው ዓለም ለማድረስ ማኅበራዊ ብዙኃንን መጠቀም ይኖርብናል። ሚዲያዎቹን እንደባሕርያቸው አገልጋዮችና ምእመናን ሊጠቀሙባቸው ይገባል። ይህ ሲሆን የበዓላቱን ዓለም አቀፋዊ ደረጃ የላቀ ያደርገዋል። ጌታችን እስከ ዓለም ዳርቻ እንዲደርስ ያዘዘውን የስብከተ ወንጌልና የምስክርነት አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ አመቺ ነው። "የክርስቶስ ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል" ተብሎ የተነገረውን ማስታወስ ይገባል።

**የበዓላት ማክበሪያ አደባባዮች ከበዓላቱ ቀናት ውጪ ጦም ውለው ጦም የሚያድሩ፣ ቆሽሸው የሚታዩ፣ ለወንጀል ማስፋፊያ የሚሆኑ፣ ለሕገ ወጥ ንግድ መናኸሪያ የሚሆኑ ወይም ባለሀብቶች በገቡ በወጡ ቁጥር የሚጎመጁባቸው ቦታዎች ከሆኑ ፈተና ያጋጥማቸዋል።**

በሀገር ውስጥ የምንጠቀምባቸውን ብቻ ሳይሆን ከሀገር ውጪ ያሉ የብሮድካስት ሚዲያዎችንና የኅትመት ሚዲያዎችን የምንጠቀምበትን አቅም ማጎልበትም ያስፈልጋል። እንዲህ ካደረግን ወንጌል የምናስተምርባቸውን አደባባዮች አበዛን ማለት ነው።

## አደባባዮችን ማስፋፋት

በዓላት ማክበሪያ አደባባዮችን በተለያዩ ምክንያቶች በማጣት ማክበር ለሚቸገሩ ወገኖቻችን በዓላቱን የሚያከብሩበትን ዕድል ማመቻቸት ያስፈልጋል። በዐደባባይ በዓላት መሳተፍ አልቻሉም ማለት በቤታቸው ለመወሰን፣ በሥጋዊ ሥራዎች ለመጠመድ አጋለጥናቸው ማለት ነው።

የአዳዲስ መንደር ነዋሪዎች በዓላትን እንዳያከብሩ ለሚያደርጉ ችግሮች ሊያጋልጡ ይችላሉ። የማክበሪያ ቦታ እጥረትን ለመቅረፍ አጥቢያዎች ኅብረት ኖሯቸው፣ ምእመናንን፣ አስተባብረው ሕጋዊ በሆነ መንገድ ፊርማ አሰባስበው ወይም በሌላ አማራጭ መንገዶች አደባባይ መጠየቅ ይገባል። ብዙ አጥቢያዎች በጋራ ሲጠይቁ ሰፋ ያለ የሚለማ አደባባይ የማግኘት ዕድልም ያገኛሉ። በተከሠተው የመሬት ውድነትና የመሬት አጠቃቀም መወሳሰብ ምክንያት አጥቢያዎች ለየራሳቸው በዓል ማክበሪያ አደባባይ ቢጠይቁ አዎንታዊ መልስ ሊያገኙ የሚችሉበት ዕድል ጠባብ ነው። ስለዚህ በአዲስ አበባ ጃን ሜዳ እንዳለውና ብዙ አጥቢያዎች እንደሚስተናገዱበት ያለ አደባባይ ለማግኘት በጋራ መጠየቅ ይጠቅማል።

በተለይ በጋራ መኖሪያ ቤቶችና በአዳዲስ የሠፈራ አካባቢዎች የሚገኙ አጥቢያዎች ተባብረው ኅብረት በመፍጠር መንቀሳቀስ አለባቸው። እንዲህ ካላደረጉ የአደባባይ በዓላትን ማክበር የማይችሉበት፣ በቤታቸው ብቻ ተወስነው በሚዲያ እያዩ ለማክበር የሚገደዱበት ሁኔታ ይፈጠራል። በተለይ በአዲስ አበባ ደመራን በመስቀል አደባባይ ተገኝቶ የሚያከብረው ምእመን ሊቀንስ ይችላል። መኖሪያ መንደሮች ከከተማው ዳርቻ እየተስፋፉ በመሆኑ በቦታው ተገኝቶ ለማክበር በትራንስፖርት ችግር ምክንያት ላያከብሩ ይችላሉ። ስለዚህ ከከተማ ወጣ ያሉ አዳዲስ መንደሮች የደመራ ማክበሪያ ቦታ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማሰብ ይኖርባቸዋል።

## አደባባዮችን ማልማት

መሬት ከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል። ከዚህ የተነሣ ለበዓላት ተብለው የሚተው ሰፋፊ አደባባዮች የተለያዩ ወገኖች ዓይን የሚጥሉባቸው እየሆኑ ነው። ለኢንቨስትመንት፣ ለእርሻ፣ ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ እየተባለ መሬት ይጠየቃል። የመሬት ይዞታን ሕጋዊ የማድረግ ብቻ ሳይሆን ይዞታን የማልማት ግዴታ እንዳለብን መረዳት ይገባል።

የበዓላት ማክበሪያ አደባባዮች ከበዓላቱ ቀናት ውጪ ጦም ውለው ጦም የሚያድሩ፣ ቆሽሸው የሚታዩ፣ ለወንጀል ማስፋፊያ የሚሆኑ፣ ለሕገ ወጥ ንግድ መናኸሪያ የሚሆኑ ወይም ባለሀብቶች በገቡ በወጡ ቁጥር የሚጎመጁባቸው ቦታዎች ከሆኑ ፈተና

ያጋጥማቸዋል:: ይህ እንዳይሆን ክርስቲያኖች እንዲያለሟቸው ሊሰጣቸው ይገባል ነበር:: መንግሥት አልምቶ ይዞታነቱን ከቤተ ክርስቲያን የሚነጥቅ ከሆነ ፈተና እንዳያጋጥመንና ክርስቲያኖች ቦታውን ባለማልማታችን እንዳንተች ቤተ ክርስቲያን እንድታለማው ማገዝ ይገባል::

ቤተ ክርስቲያን በየአካባቢው የሚገኙትን የአደባባይ በዓላት ማክበሪያ ቦታዎች ከበዓላት ማክበሪያነት ባሻገር ተጨማሪ አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጎ ማልማት ይጠበቅባታል:: በተለይ ዜጎችን ሁሉ የሚጠቅሙ ማኅበራዊ አገልግሎት መስጫ ሆነው የሚለሙበት አሠራርን መዘርጋት አለባት:: እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ፣ ባለሙያዎችን ባሳተፈ መንገድ፣ የሀገሪቱን ሕግ ባከበረ መንገድ ማልማቱ የሚገጥመውን ፈተና ይቀንሳል:: ከዚያ ባለፈ ደግሞ የሚለማበት መንገድ ለበዓላቱ ተጨማሪ የድምቀት ዕድል እንዲሰጥ ማድረግም ጥበበኛ መሆን ነው::

## በፍቅር የሚጣራ በዓል ማድረግ

የአደባባይ በዓላት መስበኪያ ናቸው:: የምስክርነት ሥራ የምንሠራባቸው በመሆናቸው ሁሉን ለክርስቶስ ለማስገዛት ከፈለግን አገልግሎታችን ወዳጅን የሚያስደስት እንዲሆን መትጋት ያስፈልጋል:: ከግጭትና ከትርምስ የተጠበቀ ሰላማዊ ማድረግ ያስፈልጋል:: ማራኪ ማድረግም ብልህነት ነው:: ይህም እኛ ባላሰብነው መንገድ ብዙዎች ለክርስቶስ ቤተሰቦች ፍቅር እንዲያድርባቸው ያደርጋል:: ብዙዎች ሾላ ላይ ተቀምጠው ሊያዩን ስለሚችሉ ፍቅራችንና ትጋታችን ሊጠራቸው ይችላል:: በዓሉን የክርክር፣ የመበሻሸቅ፣ የፉክክር ላለማድረግ መጠንቀቅ አለብን:: የማያስቆጣ፣ ሌሎችን የማይጋፋ እንዲሆን መሥራት ያስፈልጋል:: በፍቅር የሚጣራ መሆን ስላለበት ‹‹እዩ›› ሳይባል የሚታይ፣ ‹‹ስሙ›› ሳይባል የሚሰማ፣ ‹‹ላስረዳችሁ›› ሳይባል የሚተረጎም መሆን ይኖርበታል::

## በማኅበረሰቡ የሚከወኑ ተጨማሪ ነገሮች /extension/ እየተቈጣጠሩ ማበልጸግ

ሕዝበ ክርስቲያኑ በራሱ የአከባበር ባህልና ቍጥጥር ሥር የሚያከብራቸውን ለምሳሌ በዓለ ደብረ ታቦር፣ ግንቦት ልደታና የመሳሳሉ በአደባባይ የሚከበሩ በዓላትን ጨምሮ የቤተ ክርስቲያን መዋቅር በተቻለ መጠን ክርስቲያናዊ ትውፊታቸው የበለጠ ጎልቶ እንዲወጣ ለማድረግ ጥረት ከማድረግ ጎን ለጎን መቈጣጠርም ይገባል:: ያፈነገጡ ነገሮችን ለማስተካከልም መዋቅሩ ጥረት ማድረግ ይገባዋል::

## የማይገቡ ነገሮችን መቀነስ ወይም ማስወገድ

ለወንጌል አገልግሎት የተሠሩ በዓላት ከዓላማቸው ዝንፍ እንዳይሉ ኦርቶዶክሳውያን ሊጠነቀቁላቸው ይገባል:: የበዓላቱ መልክና፣ የሚተላለፈው መልእክት በጨው የተቀመመ መሆን አለበት:: ለወንጌል እንግዳ የሆኑ ሰዎች ሰምተው እንዲማረኩ፣ አስቀድመው የተማሩትም በተማሩት ጸንተው እንዲያፈሩ የሚያደርግ ዝግጅት ሊሆን ይገባል:: ጸጋ መልበሻ፣ በረከት፣ ረድኤት ማግኛ እንዲሆኑ አስቦ መሥራት ያስፈልጋል:: ከውጪ የሚመጡ ክርስቲያን ወገኖቻችን በአብያተ ክርስቲያናት መካከል መቀራረብ እንዲፈጠር አቅዶ መሥራት የበዓላቱን ዓላማ ውጤታማ ያደርገዋል::

የበዓላትን አከባባር ለመጎብኘት የሚሔዱ ወገኖች በስብከቱ መማረክ አለባቸው፤ አይተው የማድነቃቸው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ ሳይሆን ተቀጽላ ነገር ነው:: ከቅጽሉ ሌላው አካል ሊጠቀም ይችላል:: ሰዎች ወንጌልን እንዲገፉ ምክንያት መሆን የለባቸውም:: በተለይ ገንዘብን በማይገባ መንገድ ከታዳሚዎች ለመሰብሰብ የሚሹ አካላት የሚገሠፁበት አሠራር በነገዋ ቤተ ክርስቲያን መዘርጋት አለበት:: የማይገቡ ሥጋዊ ሥራዎች፣ ወንጀሎች፣ የኃጢአት ተግባራት በበዓላት አደባባይ እንዳይስፋፉ በጥብቅ መቈጣጠር የነገዋ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት ሊሆን ይገባል:: በአደባባይ በዓላቱ ጊዜ ከታዳሚዎች ፍላጎት የተነሳ የሚያስፈልጉ ነገሮች፣ ወይም ቤተ ክርስቲያን ምእመናንን በማስጨነቅ ሳይሆን በፍቅር እንዲያደርጉት የምትጠይቀው ለአገልግሎት የሚያስፈልግ ገቢ ካለም ለይቶ ማካሄድ ያስፈልጋል::

በአደባባይ በዓላት ለገበያ የሚቀርቡ ነገሮች በተቻለ መጠን ለበዓሉ ግብዓት፣ ለአክባሪዎች ደስታና ዕረፍት የሚሰጡ ነገሮች ብቻ እንዲሆኑ ለማድረግ ይገባል:: ንዋየ ቅድሳት፣ መንፈሳዊ መጻሕፍት፣ ለቤተክርስያን መባእ ሆነው ሊሰጡ የሚችሉ ነገሮች፣ አልባሳትን ጨምሮ ከበዓሉ ጋር የተያያዙ የባህል ዕቃዎች፣ መንፈሳዊ መልእክት የሚያስተላልፉ ልዩ ልዩ ነገሮች፣ ለተሳታፊዎች ጊዜያዊ ብርታት የሚሰጡ የሚበሉና የሚጠጡ ነገሮች ወዘተ ለሽያጭ ሲቀርቡ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: በተቻለ መጠን በዚህ አገልግሎትም የቤተክርስቲያኒቱ ተቋማት የሚሠሩት የሚያቀላጥፉት ቢሆን ተጨማሪ ገቢ ማግኛ ይሆናል:: በዓሉን መደበኛ ገበያ ለማድረግ የሚሹትን ከሚመለከታቸው ጋር ተቀናጅቶ ሥርዓት ማስያዝ በዓላቱን ከትርምስና ትኩረት ከመነፈግ ያድናል::

የቤተ ክርስቲያን አባቶችን የአገልግሎት ልብ በማይሰርቅ፣ ዋናውንም አገልግሎት በማያዘናጋ መንገድ ካልተፈጸመ ጉዳቱ ቀላል አይሆንም:: የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወንጌልን ስበኩ ከሚለው ዐዋጅ በስተቀር ሊገዛቸው የሚገባ ሕግ በበዓላቱ ሥርዓት ውስጥ መኖር አይገባውም:: ስለገንዘብ ማሰባሰብ፣ ስለበዓላቱ ድግስ፣ ስለቱሪዝም መስፋፋት፣ ስለባህል ልማት እንዲጨነቁ ክፍተት መፍጠር አይገባም:: ለዚህም “የእግዚአብሔር ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም” (የሐዋ.፮፥፪) ያሉትን የሐዋርያትን ቃል መመሪያ ማድረግ ያስፈልጋል::⌖

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# «የሰላምታ ደብዳቤ»

**ቀሰስ ሽፈራው አስራቴ**

ይድረስ እናትም፣ አባትም፣ እኅትም፣ ወንድምም ሆነሽ ሕይወትን እያለማመድሽ ላሳደግሽኝና ለምታሳድጊኝ አለኝታዬ “ሐመር መጽሔት” የሰማይ ርቀቱን፣ የመሬት ስፋቱን፣ የፀሐይ ሙቀቱን፣ የኮከብ ብዛቱን፣ የጨረቃ ድምቀቱን ያክል እንደምን ውለሽ አድረሻል? እንደምንስ ከርመሻል?
እኔ ከውዷ የሕይወት መንገዴ ከሆንሽው ከአንቺ አሳብና ናፍቆት በስተቀር የአባትነት ፍቅሩን ያሳየሽኝ የሁላችንም ፈጣሪ ቅዱስ እግዚአብሔር እናታችን አማላጂቱ ቅድስት ድንግል ማርያም አዛኝቱ እና ባለሟሎቹ ቅዱሳን ሁሉ ክብርና ምስጋና ይድረሳቸው በጣም ደኅና ነኝ።

ሐመርዬ እንደምታውቂው በስምንተኛው ሺሕ የሰላምታ ደብዳቤ መጻጻፍ በቀረበት ዘመን ሰላምታዬን እና ናፍቆቴን ጽፌ ስልክልሽ በጣም ትገረሚ ይሆናል። ግን የመቅረትሽን ወይም የመጥፋትሽን ጉዳይ ባሰብሁ ቍጥር ልቤ ስለሚጨነቅና ስለሚሽበር ስልክ ብደውልልሽ የልቤ ሳይደርስ እና አሳቤን ሳልጨርስ ኔትወርክ ይለየናል ብዬ መሆኑን ትረጂዋለሽ ብዬ አምናለሁ። ሐመርዬ ግን ከተለያየን ድፍን ሁለት ዓመት ሊሆነን እንደሆነ አስበሽዋል? መቼም ይህን ያህል ጊዜ አስችሎሽ ትጠፊያለሽ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር።
ድምፅሽ የጠፋው በሕይወት እያለሽ፣ የሚጨክን አንጀት አግኝተሽ ከሆነ የተሰወርሽው በጣም ባይሆንም የማዝንብሽ ይመስለኛል። እንዴት በዚህ በመከራ ጊዜ ትተሽን ትጠፊያለሽ እያልኩ ሆዴን ባር ባር ይለው ነበር።

ሰው እንዴት ወልዶ ያሳደገውን ትቶ ይጠፋል? ይህን ያህል በድያለሁ ማለት ነው? ቢያንስ እኔ ከገጠሪቱ ክፍል ከቆላማው ቦታ ተወልጄ ፍየሎችና በጎች ሳግድ፣ ማማ ላይ ሆኜ በወንጭፌ ማሽላ ስጠብቅ ያደግሁና ምንም የማላውቅ ዱዳ በቀለም ትምህርት ምክንያት ወደ ከተሜነቱ ብቅ ባልሁ፣ ገና የግቢ ጉባኤ ልጅ በነበርኩበት ጊዜ ማለትም በ1994 ዓ.ም ጀምሮ የማላውቀውን እኔን ወልደሽ አሳድገሽ፡ አስተምረሽ ለድቁና፡ ለቅስና ብሎም በየዐውደ ምሕረቱ የትሩፋት አገልጋይ ያደረግሽኝ የሕይወት መንገዴ ስለሆነሽ በአንቺ ሳንባ ስተነፍስ ድፍን ሃያ ዓመት እንደሆነኝ ይረሳሻል ብዬ አይደለም ይህን ሁሉ የምጽፍልሽ?

አንቺ ስትርቂኝ በማን ሳንባ ልተንፍስ? ከአንቺ ጋር ሳንወያይ፣ ምክርሽን ሳልሰማ መድረክ ላይ ብቆም የሚፈጠረውን ችግር አሰበሽዋል? አንቺን አንብቤ ለማስተማር ካልተዘጋጀሁ ለችግር ስለምጋለጥ አንችንም እኔንም ያስነቅፈናል። እንደምታውቂው ሰው የመሰልኩት በአንቺው ነው። ያለ አንቺ ድጋፍ ባዶ ስልቻ እንደሆንሁ ዘነጋሽው ማለት ነው? አንድ ምሳሌ ልንገርሽ።

አንድ ትልቅ አባት በተገኙበት የሰርክ ጉባኤ ላይ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ድብልቅልቅ እያደረገ ሲያስተምር የነበረ አንድ ያልተማረ የእኔው ቢጤ ወጣት በቦታው የነበሩት ትልቅ አባት ሁኔታው ስላስቆጫቸው አስተምሮ ሲጨርስ አስጠሩና “ልጄ! እንዲያው የሆነው ይሁንና ትምህርት ትማራለህ?” ብለው ጠየቁት።

ወጣቱም “አልማርም” አላቸው። “ለምን?” አሉት። “የምበላው ስለሌለኝ” አላቸው። “ታዲያ ምን እየበላህ ደነቆርክ?” ብለው ቁጭታቸውን ገለጹ ይባላል። አንቺ የሚጠቅመኝን ስለምታውቂ ሳታፍሪ፣ ሳትፈሪ የጎደለኝን የምትነግሪኝ መልካም እናት እኮ ነሽ። የኔታ ነገሩኝ ብለሽ ያጫወትሽኝ አይረሳኝም። ይኸውም ማንበብ፣ መጠየቅ፣ መመራመር ትልቅ ሰው እንደሚያደርግ የነገርሽኝ እኮ አንቺው የእኔዋ የዕውቀትም፣ የእምነትም መሠረት የሆንሽው ነሽ። ዛሬስ? ነገስ? የጎደለኝን የሚነግረኝ በማጣት ቀለም ካልቈጠሩት መካከል አንዱ እንደሆነ ይቅር ብለሽ ነውን? “ያስተማርሁ መስሎኝ ነፍሳትን ሁሉ እያጠፋሁ፣ የሰበሰብኩ መስሎኝ እየበተንኩ እንድኖር ስለማትፈልጊ እባክሽ በቶሎ ነይ?” እኔ እኮ “ሰንብቶ ተማሪ እንጂ ሰንብቶ መራሪ” መሆን የማልፈልግ የሃያ ዓመት ጎልማሳ ልጅሽ ነኝ። ታዲያ የሃያ ዓመት ልጅ ምንስ ቢበድል ይህን ያህል ይረሳል? ግን አስችሎሽ ነው? እኔ ግን ድርጊትሽ ገርሞኛል!!!

አንቺን ባስቀይምሽም ነቢዩ እንደተናገረው “ ጽዮን ግን ‘እግዚአብሔር ትቶኛል ጌታም ረስቶኛል አለች’። በውኑ ሴት ልጇን ትረሳለችን? ከማኅፀንዋ ለተወለደውስ አትራራምን? ሴት ይህን ብትረሳ እኔ ግን አንቺን አልረሳሽም። እነሆ እኔ በእጄ ግንቦችሽን ሣልሁ፤ አንቺም ሁልጊዜ በፊቴ ነሽ። ከአፈረሱሽ በኋላ ፈጥነሽ ትታነጺያለሽ ያፈረሱሽ ከአንቺ ይወጣሉ፤ ዐይንሽን አንሥተሽ በዙሪያሽ ተመልከቺ፣ እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ወደ አንቺ ይመጣሉ” (ኢሳ.፵፱፥፲፬- ፲፰) አምላኳ እንዳጽናናት የምታጽናኝኝ ይመስለኝ ነበር።

የሕይወት መንገዴ እንደ እናቴም የሆንሽው ሐመርዬ አየሽ የሆዴን አውጥቼ ያመመኝን፣ የተሰማኝን፣ ቅሬታዬን፣ ጉዳቴን፣ ናፍቆቴን መናገር የቻልኩት ድሮ መለያየት፥ ዘረኝነት፥ ኑፋቄ፥ መከዳዳት፥ መረሳሳት፥ የሚባሉ ወረርሽኝ በሽታዎች በማይታወቁበት በዚያ በፍቅር ዘመን ሀገራችን ኢትዮጵያ ከእምነት ማማ ላይ በነበረችበት ዘመን ትጠቀምበት በነበረው ሰፊ የደብዳቤ አውድማ ላይ ብዕርና ብራናን በማግኘቴ ነው።
የሚያለያየንን “ዛሬን” አሶግዶ የሚያግባባንን “መልካሙን ትናንት” እንዲያመጣልን “ሐመርዬ” ባለሽበት ሆነሽ ብትጸልይ፣ ብታሳስቢ እና ለእኛም ብታሳስቢልን ይሻላልና በደኅናሽ ከሆነ

ባትጠፊ እኔንም ደስ እንዲለኝ የሆድሽን በሆድሽ ይዘሽ ብትመጪ መልካም ነው:: "ሐመር" የሰላምታ ደብዳቤ ብዬ ጀመርኩና ወቀሳዬን አበዛሁብሽ አይደል? ስትመጪ በይቅርታ የምክስሽ ይመስለኛል ብቻ ነይልኝ እንደ እኔ የሚናፍቁ ብዙ ናቸውና ለእነሱም ነይላቸው:: ሐመርዬ እንዲህ የምጽፈው ሐዋርያዊው ቅዱስ አትናቴዎስ በቅዳሴው "እንደበትን እየተናገሩበት ሊወቅሱት ይገባል" በማለት እንደተናገረው ራሴን ለመውቀስ እንጂ ጥፋቴን በአንቺ ለማመካኘት አይደለም:: እንዲያውም ልንገርሽ የበደልኩሽ እኔ ብቻ ከሆንሁ የሚያከብሩሽን አስበሽ የእኔን በደል ብትረሺው ይሻልሻል::

እንዲህ በማለት ጽፌ የምወቅስሽ እናት፣ ሕይወቴ እና መንገዴ በመሆንሽ ናፍቆቴ ስለጨመረ ነውና እንዳይከፋሽ::

በነገራችን ላይ ከእኔ ለመራቅ ያበቃሽ ኃጢአቴን ሳላስበው የቀረሁ አይምሰልሽ::

**አንቺም ምንድን ነው ትይኝ እንደሆነ፡-**

፩ኛ. አንቺን የመሰለ ገበታ ዘርግቼ ተመግቤ ሳልጨርስ ፌስ ቡክ ላይ ስላየሽኝ ልብሽ አዝኖብኝ ሊሆን ይችላል::

፪ኛ. በየወሩ ስትመጪ የማስታውስሽ እና እንደነገሩ የምቀበልሽ በመጣሽ በወሩ መጨረሻ ስለነበረ ስለአጉላላሁሽ ተቀይመሽ::

፫ኛ. በጠረንጴዛው ሥር አንቺና ብዙ ጠቀሜታ የሌለው ልቦለድ አይሉት ፓለቲካ ይዘት ያለው መጽሐፍ አንድ ላይ ተቀምጣችሁ አንቺን ገፍቼ እርሱን እያነበብኩ እውል ስለነበርና ያነበብኩትን እንደ እውነት በመቊጠር ሌሎችን ለማሳመን እከራከር ስለነበር::

፬ኛ. አንቺን እገልጥሽ የነበረው ከአልጋዬ ተኝቼ ወይም ከሦፋዬ ተጋድሜ እንቅልፍ እንዲመጣልኝ ስለነበረ በዚያ አዝነሽ ወር ጠብቁ ብሔድስ መች ያነበኝና ብለሽ ይሆናል::

፭ኛ. የእናትነት ፍቅርሽን ለሌሎች መግለጥ ሲገባኝ ስለደበቅሁ መክሊቱን እንደ ቀበረው ገብር ኃካይ ቈጥረሽኝ ቢሆንስ ብዬ እሰጋለሁ::

፮ኛ. ከአንቺ ጋር ስናወጋ ልቤ በአሳብ እየዋተተ፣ ዓይኔ ንባቡን እያንበለበለው፣ አፌ ቀለሙን እየነዳው ቢሆንም ሰብሰብ ብሎ መከታተል ሲኖርበት ልቤ ዕቃ ከማሰናዳት የማያርፍ በመሆኑ እስቲ ትንሽ ተሰውሬ ልቆይና ጥቅምና ጉዳቴን ይረዳው ብለሽ ይሆናል::

ሐመርዬ እኔም፣ እግዚአብሔርም፣ አንቺም በምናውቀው ስንፍና ምክንያት ከመታተም ብትዘገይም አሁን ግን በቶሎ ነይልኝ:: ከእንግዲህም በጥንቃቄ አነብብሻለሁ:: ጭስ እንዳይተንብሽ፣ አቧራ እንዳይበንብሽ ከተከበረ ቦታ አስቀምጥሻለሁ:: የነበረ ነገር የሚታወቀው የጠፋ ጊዜ ነው የተባለው በእኔ ስለደረሰ በቶሎ ነይና ችግሬን አስወግጅልኝ::

ግን እኮ እናት የሕይወት መንገድ ነችና የሚጨክን ልብ የላትም:: ይህንንም ይቅር የማለት አቅም አላት:: ይብላኝ እንጂ ለእኔ ይቅርታ ገደሉ ለሆነብኝ:: ማዘን የሚገባው ዕውቀትሽንም፣ የምትነግሪንን መንፈሳዊ ሕይወትንም ተምሮ በተግባር መግለጥ እንደሰማይ ለራቀብኝ ለእኔ ነው:: እናም እባክሽን እንደጠፋው ልጅ ይቅር የሚለኝን፣ አቅፎ የሚስመኝን እና የሚያጽናናኝን እፈልጋለሁና ነይልኝ:: አግኝቼሽም ማሪኝ ልበልሽ:: አንቺም ማሪኝና በፍቅር እያነበብኩ መንፈሳዊ ሕይወቴን ላለምልም::

"ላለመስማማት የተስማሙትን" እንዴት አስተምረሽ እንደለቀቅሽልኝ ረሳሽውና አንቺው ላለመስማማት ተስማማሽ እንዴ? ኧረ አይሆንም:: እኮ በአንቺ ምን ያላየሁት ነገር አለ:: እኔ የሰው ልጅ መነሻ ከሌለው መገስገሻና መድረሻ ያጣል እያልሁ የምሰማሽ ከመንገደኛው ጀምሬ ነበር:: አንቺ ለእኔ ቁም ነገሬ እኮ ነሽ::

ፊደል፣ ወይም መጽሔት አእምሮዬ ነሽ ከምሥጢረ ሥላሴ ጀምረሽ እስከ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ሥርዓት አምልኮውን፣ ዶግማና ቀኖናውን፣ የምትመግቢኝ የዕለት ጉርሴ፣ የዓመት ልብሴ ነሽ፣ ነበርሽም:: አንቺ ለሰው አዛኝ ነበርሽና ተጎሳቁዬ ብታይኝ ትጎኛለሽ:: ስለአንቺ ስንቱን ልናገር? ኢትዮጵያን ብሎም ዓለምን ከነምንነቷ ሳይብሽ የኖርኩ ወደ ፊትም የማይብሽ መስታወቴ ነሽ::

ጉዳዬ፣ ናፍቆቴ እና ብሶቴ አንቺ ብቻ ሳትሆኚ "ከዓውደ ሃይማኖት፣ ከቤተ አብርሃም፣ ከምሥጢሬን ላካፍላችሁ፣ ከሕፃናት ዐምድ ለይቶ ያለ እረኛ ከተወኝ "ከስምዐ ጽድቅም" እንጂ:: በእርሱ ላይ የብሶትና የናፍቆት አሳቤን ላነሳበት አስቤ የነበረ ቢሆንም ትዝ ሲለኝ አንቺ በቀረሽበት ምክንያት የቀረ ስለመሰለኝ ምሬዋለሁ:: ይህ ደብዳቤዬ እንደደረሰሽ ለእሱም አሰሚልኝ:: የጻፍኩትን ብሶት አንብቦ አብሮሽ ካልመጣ ደብዳቤ የምጽፍለት ሁለተኛው አካል እርሱ ሳይሆን አይቀርም::

በተረፈ የቀረውን ስንገናኝ የልብ የልባችንን እንጨዋወትና ይወጣልናል:: በዓይነ ሕሊና እንደተነጋገርን በዓይነ ሥጋ ለመተያየት ያብቃን:: አሜን!! ✥

የሁል ጊዜ ናፍቆት የሆንሽብኝ ልጅሽ!!

## በዝግጅት ክፍሉ

**የተከበራችሁ አንባብያን በጥያቄዎቻችሁ መልስ ዓምዳችን ከጽዋ ማኅበር ጋር የተያያዘ ጉዳይ ከእናንተ ከአንባብያን የቀረቡልንን ጥያቄዎች ይመልሱልን ዘንድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤቶች ማደራጃ መምሪያ ማኅበረ ቅዱሳን መደበኛ መምህር የሆኑትን አባ ፍቅር ማርያምን ጋብዘናቸዋል። ጥያቄያችንን ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነው ከእኛ ጋር ያደረጉትን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል። መልካም ንባብ።**



አባ ፍቅረ ማርያም

**ሐመር መጽሔት፡-** የጽዋ ማኅበር ማለት ምን ማለት ነው?

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** የጽዋ ማኅበር ማለት ኅብረት፣ አንድነት ማለት ነው። ይህ ኅብረት ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ የነበረ ሲሆን የቤተ እስራኤል አንድነት ምሳሌም ነው። ሕዝበ እስራኤል በምድረ በዳ ሲጓዙ በአንድ ሙሴ ይመሩ፣ በአንድ ማኅበርም ይመገቡ ነበር። እግዚብሔር አምላካችን በብሉይ ኪዳን በሙሴ መጋቢነት የነበረውን የእስራኤልን አንድነት ለሐዲስ ኪዳኗ አማናዊት ቤተ ክርስቲያን ምሳሌ አድርጎ ገልጾታል። በዚህም መሠረት የጽዋ ማኅበር ማለት ኅብረት፣ አንድነት እንደሆነ እንረዳለን።

በሐዲስ ኪዳንም ራሱ ባለቤቱ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረተው የሐዋርያት ኅብረት፣ አንድነት ነው። ሐዋርያት ጌታችን የመሠረተውን ማኅበር አስቀጥለውታል፤ በኋላም ማኅበሩ እየሰፋና እያደገ ሲመጣ ለአስተዳደር ይመች ዘንድ ሰባቱን ዲያቆናት ሹመውላቸዋል። ከእነርሱም መካከል እስጢፋኖስን ሊቀ ዲያቆን አድርገው በመሾም ማኅበሩ በሊቀ ዲያቆኑ በእስጢፋኖስ እንዲመራ አድርገዋል። ይህንም ታሪክ የሐዋርያትን ሥራ የጻፈልን ቅዱስ ሉቃስ "ዐሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ሕዝቡን ሁሉ ጠርተው እንዲህ አሏቸው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ አይደለም። ወንድሞቻችን ሆይ ከእናንተ ወገን በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብ የሞላባቸውን ሰባት ሰዎችን ምረጡ፤ ለዚህ ሥራም እንሾምላችኋለን። እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማስተማር እንተጋለን። ይህም ነገር በእነርሱ ዘንድ የተወደደ ሆነ፣ ሃይማኖቱ የቀናና መንፈስ ቅዱስ ያደረበትን ሰው እስጢፋኖስን፣ ፊልጶስን፣ ጵሮኮሮስን፣ ኒቃሮናን፣ ጢሞናን፣ ጰርሜናን፣ ወደ ይሁዲነት የተመለሰውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሟቸው፤ ጸልየውም እጃቸውን በራሳቸው ላይ ጫኑ" (ሐዋ. ፮፥፪-፮) በማለት ጽፎልናል።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ተገልጦ ጠቅሰን ያቀረብነው ታሪክ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመሠረተውን ማኅበር፣ ሐዋርያትም አስፍተውና ጠብቀው ለእነ እስጢፋኖስ ያስተላለፉት ነው። ይህ ማኅበር ማኅበረ እስጢፋኖስ እየተባለ ይጠራ ነበር። ስለዚህ የጽዋ ማኅበር ማለት በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በእመቤታችን በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክት፣ በቅዱሳን ጻድቃን፣ በቅዱሳን ሰማዕታት ስም የሚደረግ የምእመናን ስብስብ ወይም አንድነት ማለት ነው። ይህም ማኅበር የቅዱሳኑ መታሰቢያ የሚደረግበት ማኅበር ነው። በቅዱሳኑ ስም መታሰቢያን ለሚያደርጉ ደግሞ ነቢየ እግዚአብሔር ሰሎሞን "የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው" (ምሳ.፲፥፯) በማለት እንደተናገረው በረከት ያገኙበታል።

**ሐመር መጽሔት፡-** የጽዋ ማኅበርተኞች በአንድ ላይ የሚቀምሱት ሰአልናከ የሚባለው ጸበልና ጸዲቅ ትርጉሙ ምንድን ነው?

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** ሰአልናከ ማለት የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ለመንህ ማለት ነው። ይህም ሥልጣነ ክህነት ባለው ካህን ብቻ የሚጸለይ ጸሎት ነው። በምእመናን አይጸለይም ምክንያቱም በየመሐሉ "ባርክ ለነ ክርስቶስ አምላክነ ዘንተ ኅብተ፤ ወዘንተ ጽዋዐ፣ ቀድስ ለነ ክርስቶስ አምላክነ ዘንተ ኅብስተ፤ ወዘንተ ጽዋዐ" እየተባለ በካህን ብቻ የሚፈጸም ቡራኬ አለው። ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችው ከመዝሙረ ዳዊት የተውጣጣ ጸሎትም አለው። ኅብስቱንና ጽዋውን ከሌላው ምግብ ልዩ የሚያደርገው ይህ ጸሎት ስለሚጸለይበት ነው። ይህም በካህኑ ጸሎት ስመ አምላክ ተጠርቶበት ከተባረከ በኋላ የማኅበሩ አባላት ብቻ የሚቀምሱት ነው። ይህን ጸሎት ዲያቆንም ቢሆን አይጸልየውም። ምክንያቱም ቡራኬ ቅስናና ከዚያ በላይ ሥልጣነ ክህነት ባለው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሚፈጸም ስለሆነ ነው።

በጽዋ ማኅበር ላይ የሰአልናከ ጸሎት ይጸለያል። የሚጸለይበት ምክንያት በጽዋ ማኅበሩ የተሰበሰቡት ሰዎች እንደ ዕቁብና እድር ለሥጋዊ መረዳዳት ብቻ ሳይሆን ሰማያዊውን ርስት ሊወርሱ ነውና የቀረበው ኅብስትና ወይን እንዲባረክ፣ ማኅበርተኞቹ

አንድነታቸው እንዲጸና፣ ፍጻሜቸውን እንዲያሳምርላቸው የሚጸለይ ጸሎት ነው፡፡ ማኅበርተኞች በጋራ የሚቀምሱት ጸበልና ጸዲቅ ሰአልናከ የሚል ስያሜ የተሰጠውም ሰአልናከ የሚባለው ጸሎት የሚጸለይበት በመሆኑ ነው፡፡

የሰአልናከ ጸሎት የተጸለየበትን ጸበልና ጸዲቅ የሚቀምሱት የጽዋ ማኅበሩ አባል የሆኑት ብቻ ናቸው፡፡ ለሥጋ ወደሙ ማቅረቢያ ደጅ መጽኚያም ነው፡፡ እርሱ ራሱ ግን ሥጋ ወደሙ አይደለም፡፡ አንዳንድ ሰዎች በተሳሳተ ግንዛቤ እንደ ሥጋ ወደሙ አድርገው ይቈጥሩታል፡፡ በግለሰብ ቤት የሚዘጋጅ ጸዲቅና ጸበል መቼም ቢሆን ሥጋ ወደሙ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ግን በተሰበሰቡበት ቅዱስ ስም አምነው፣ ቅዱሱንም ለአማናዊው ሥጋና ደም ያበቃቸው ዘንድ እየተማፀኑ ቢቀምሱት ለአማናዊው ሥጋ ወደሙ እንዲበቁ ያደርጋቸዋል፡፡

**ሐመር መጽሔት፡-** አባታችን ሰአልናከ ምግብ ከተቀመሰ በኋላ ይበላል ወይስ አይበላም?

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** የሰአልናከ ትውፊታዊ ሥርዓት ምግብ ሳይበላ እንዲቀመስ ነው የተሠራው፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተጻፈ ሕግ እንዳላት ሁሉ ሳይጻፍ በትውፊት የምትጠብቀው ሕግም አላት፡፡ ይህ ሰአልናከ በመጽሐፍ ባይጻፍም በትውፊታዊው ሕግ ከምግብ በፊት የሚመገቡት ነው፡፡ ምክንያቱም አስቀድሞ እንደተገለጸው ለሥጋ ወደሙ መዘጋጃ፣ ደጅ መጽኛ ነው ብለናልና፣ የጸሎት ክፍሉም የተለየ ነውና ከምግብ በፊት በባዶ ሆድ ሆነው እንዲቀምሱት የተሠራው፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይበላል አይበላም ብለው ማኅበርተኞቹ እንደ ዕውቀት ቢነሣም ሊያከራክርና የሰፋ ልዩነት ሊፈጥር ግን አይገባም፡፡ የሐዋርያትን ትምህርት መሠረት ካደረግን ልዩነታችንን የሚያጠብልን ሥርዓት ሠርተውልናል፡፡ "በጾም ምክንያት ይበላል አይበላም በማለት በተለያያችሁ ጊዜ ለጾም አድሉ" ብለው ሥርዓት ሠርተውልናልና ለጾም ሲሆን ለጾም አድሉ ከተባልን ይህንም በዚያው መልኩ ተረድተነው ከምግብ በፊት መመገብ እንዳለባቸው መረዳት ይገባቸዋል፡፡

**ሐመር መጽሔት፡-** የጽዋ ማኅበርተኞች ሠራተኞች ቢሆኑ ወደ እሑድ ከማዛወር በዋዜማው ቀን ከአሥራ አንድ ሰዓት ጀምሮ የጽዋ መርሐ ግብር ማካሔድ ይችላሉ? ይህን ያነሣንበት ምክንያት ጽዋ ማታ ከደጋሹ ቤት ወደ ተቀባዩ ቤት አይንቀሳቀስም የሚል አሳብ ስለሚቀርብ ጽዋ ማታ ከቤት ወደ ቤት አይንቀሳቀስም የሚል የቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አለ ወይ? ይህንም አያይዘው ቢያብራሩልን፡፡

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** ቤተ ክርስቲያናችን ሦስት መቶ ስልሳ አምስቱንም ቀናት በዓላት አላት፡፡ በጌታችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፣ በቅድስት ድንግል ማርያምና በሌሎችም ቅዱሳን ስም የሚታሰቡ ከወር ወር፣ ከዓመት ዓመት የምታከብራቸው በዓላት አሏት፡፡ እነዚህም በዓላት የቅዱሳኑ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔር ለቅዱሳኑና የቅዱሳኑን መታሰቢያ ለሚያደርጉ ምእመናን ያደላቸው ጸጋዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ ቅዱሱ/ቅድስቲቱ ይታሰብበት/ትታሰብበት ዘንድ ቤተ ክርስቲያን በወሰነችው ዕለት ቢከበር እጅግ የተሻለ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ በ፳፩ የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የመታሰቢያ በዓል ነው፡፡ ይህ የመታሰቢያ በዓል ማክሰኞ ቢውል መታሰብና መከበር ያለበት በዕለተ ማክሰኞ ነው፡፡ ማክሰኞ የሚውለውን ወደ ኋላ አምጥተን ወይም ወደ ፊት ወስደን እሑድ ላይ እንዲታሰብ ብናደርግ በዕለቱ እንዲታሰብ ቤተ ክርስቲያን የሠራችለት ሌላ ቅዱስ አለና በዕለቱ እንዲታሰብ የተወሰነውን ማሰብ ይገባል እንጂ ያለ መታሰቢያ ዕለቱ ቅዱሱን ማሰብ ተገቢ አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ የዚህ ዓለም ጫናው ከባድ ነውና በሥራ ጉዳይ ወይም በሌላ ምክንያት በዕለቱ ማከናወን አልችል ስንል እንዲህ ያለውን አሳብ እንደ መፍትሔ አድርገን እየወሰድነው ነው፡፡ ስለዚህ ቢቻል ከላይ የገለጥነውን መተግበር የበለጠ የተሻለ ይሆናል፡፡ ይህም በዕለቱ ማክበርን ቢከተሉና ለቀጣይ ትውልድ ቢያስተላልፉት መልካም ነው፡፡ ካልሆነ ግን በተመቻቸው ዕለት ማድረጋቸው ያን ያህል ሥርዓት የጣሱ ያህል እያሰቡ ራሳቸውን ማስጨነቅ የለባቸውም፡፡

ዕለቱን አሳልፎ ማክበርን አሳማኝና ምሥጢራዊ በሆነ መልኩ ቤተ ክርስቲያንም ተጠቅማበታለች፡፡ ለምሳሌ ቃና ዘገሊላ በምሥጢር የውኃን በዓል ከውኃ በዓል ጋር አከታትሎ ለማክበር በጥር ፲፪ እንዲከበር ወስናለች፡፡ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰርግ ቤት ተገኝቶ ውኃውን ወደ ወይን ጠጅ የቀየረው የካቲት ፳፫ ቀን እንጂ ጥር ፲፪ ቀን አይደለም፡፡ ይህ ሥርዓት በዚህ መልኩ የተሠራው ከበዓሉ ጋር ያሉ ምሥጢራት እንዲገናኙ ለማድረግ ታስቦ ነው፡፡ ዛሬም አባላቱ በዕለቱ ማክበር የማይችሉበት አስቸጋሪ ሁኔታ ካለ አሳልፈው ቢያከናውኑት ችግር የለውም፡፡ በሰሙነ ሕማማት የሚውሉ በዓላትም በትንሣኤና ከትንሣኤ በኋላ መከበራቸው በሚታሰቡበት ዕለት ማክበር ስላልተቻለ ነው፡፡

ከሥራ መልስ በዕለቱ ብናከብረውና ቢመሽ ከመሸ በኋላ ጽዋ ከቤት አይወጣም የሚባለው ግን አባቶች ያላስተማሩት፣ ቤተ ክርስቲያንም ለልጆቿ ያልነገረችው አሳብ ነው፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ጽዋ በዚህ ሰዓት ይወጣል፣ በዚህ ሰዓት አይወጣም የሚባል ነገር የለም፡፡

ማኅበርተኞች ከሥራ ጫናም ሆነ ከልዩ ልዩ ምክንያቶች በመነሣት ጽዋ ማኅበሩን በዕለቱ ቢያከናውኑት የተሻለ ነው ብለናልና ዕለቱ እንዳያልፍባቸው ከሥራ መልስ ቢያከብሩት ያለባቸውን ችግር እነርሱ፣ በስሙ የተሰበሰቡበት ቅዱስ/ ቅድስት እና እግዚአብሔር ያውቁታል፡፡ ስለዚህ ማታ ከሆነ የሚሰበሰቡት ጸሎታቸውን አድርገው፣ ዘምረው፣ ተማምረውና ጸበል ጸዲቃቸውን ቀምሰው ቢለያዩ፣ ጽዋውንም ከሰጪው ቤት ወደ ተቀባዩ ቤት ቢወስዱት ችግር የለውም፡፡ በከተራ ዕለት ታቦታቱን ወደ ባሕረ ጥምቀት የምንወስዳቸው በምሽት ነው፡፡ ምን አልባት በከተሞች አካባቢ ሥርዓቱ በጊዜ ይከናወናል እንጂ በገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን እኮ

ከመሸ ነው የሚወስዱት፡፡ ታቦተ ሕጉን በጨለማ ካወጣን ጽዋው በምሽት ቢወጣ ምን ችግር ሊኖረው ይችላል? ስለዚህ በቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ ላይ ቤተ ክርስቲያን የማታስተምረውን እየሰነቀርን ምእመናንን ማስጨነቅና ቤተ ክርስቲያንን ምንም አማራጭ የሌላት እንደሆነች አድርጎ ማስተማር አግባብነት የለውም፡፡

**ሐመር መጽሔት፡-** አባታችን ያለ ሰአልናከ ጽዋ ማኅበር ማካሔድ መቻል አለመቻሉን ቢያብራሩልን?

**አባ ፍቅረ ማርያም፡-** እዚህ ላይ የሰዎቹ የሃይማኖት ጽናት ይወስነዋል፡፡ ሰአልናከ ከላይም እንደገለጽነው ከተበላ በኋላ አይበላም፡፡ ስለዚህ በረከት ሊቀርብን አይገባም ብለው ሳይመገቡ ከዋሉ መልካም ነው፡፡ ካልሆነ ግን የግድ እስከ ማታ ጾማችሁን መዋል አለባችሁ ማለት ደግሞ ሌላ የማይገባ ሸክም ማክበድ ነውና ሰአልናከ ጸሎቱ ሳይደገም፣ ውዳሴ ማርያምና መታሰቢያው የሚደረግለትን ቅዱስ ገድል፣ ድርሳን ወይም ተአምር ጸልየው፣ የሰአልናከ ምሳሌ የሆነውን ጸበል ጻዲቅ ተቃምሰው ማኅበራቸውን ማከናወን ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ሰአልናከ ሳይኖር ጽዋ ማኅበር ማከናወን አይቻልም የሚል ትምህርት ስለሌለ ማከናወን ይችላሉ፡፡✠

**ይቆየን**

ከገጽ ፲፫ የዞረ

# የምንሠራው ከሪፖርት ባለፈ ...

እንደማይፈቱት ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ከመምህራን የሚጠበቅ አለ፤ ከተማሪዎች የሚጠበቅም አለ፤ ሁለቱ በመቀራረብ የሚፈጽሙት ተግባርም እንዲሁ፡፡ ችግሩን ከመለየት በተጨማሪ ችግር የገጠማቸው ወገኖች ከገጠማቸው ችግር ለመላቀቅ ፍላጎት ያላቸው መሆን አለመሆኑን ጠይቆ ማጣራት ያስፈልጋል፡፡ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሳርያን የመፈጸመውን ተግባር መገንዘብ የሚገባው በዚህ ጊዜ ነው፡፡

በአንድ ወቅት አንዲት የተጨነቀች ሴት ወደ ቅዱሱ አባት ሔዳ የገጠማትን ችግር አወያየችው፡፡ ሴቲቱ የአንድ ባለጸጋ ሰው ልጅ ነበረች፡፡ ከዓመታት በፊት አባቷን ከአሽከሮቹ አንዱን ካላጋባኸኝ ራሴን አጠፋለሁ ብላ አስቸግራው ነበር፡፡ አባቷ ከአንድ ልጁ እንዲህ ዓይነት ክብርን የሚነካ ጥያቄ ሲሰማ ግራ ቢጋባም አማራጭ አልነበረውም፡፡ ልጁን እንዳያጣ ስለፈራ ከፈቀደችው ሰው ጋር አጋብቷት ትኖር ነበር፡፡ አባት እና እናት የተለየ ጠባይ ላሳየችው ልጃቸው ሁል ጊዜ ይጸልዩ፣ ምክንያቱን እንዲገልጥላቸው ወደ እግዚአብሔር ያሳስቡ ነበር፡፡ በሃይማኖት እና በምግባር ታንፃ ያደገች ልጅ የአባቷን አሽከር ለጋባቻ የፈለገችው ያለ ምክንያት አልነበረም፡፡ አሽከሩ የጌታውን ልጅ ያገባት ከአንድ አስማተኛ ዘንድ ሔዶ ችግሩን አወያይቶ ባገኘው መፍትሔ ነበር፡፡ አስማተኛውም ወረቀት ጽፎ ይህን ወረቀት ይዘህ በቅርብ ጊዜ ከሞተ አረማዊ ሰው መቃብር ሔደህ ፊትህን ወደ ምዕራብ አዙረህ ቁም፤ ወረቀቱን የሚቀበልህ ይመጣል፤ በቶሎም የምትፈልገውን ታገኛለህ አለው፡፡

አሽከሩም እንደ ተባለው ወደ አረሚ መቃብር ሔዶ ፊቱን ወደ ምዕራብ አዙሮ እንደ ቆመ አስማተኛው እንደ ነገረው ሰይጣን መጥቶ ወረቀቱን ነጥቆ ወሰደበት፡፡ በመቀጠልም እግዚአብሔርን አስክዶ ክህደቱን በወረቀት ጽፎ እንዲሰጠው ጠየቀው፡፡ የባለጸጋው ሎሌም በአሳቡ ተስማምቶ የክህደት ደብዳቤውን ጽፎ ለሰይጣን ሰጠው፡፡ ሰይጣንም በባለጸጋው ሰው ልጅ ልብ ገብቶ ሲወጣ ባቱን፣ ሲገባ ደረቱን እያየች መታገሥ ስለተሳናት አባቷን ከአሽከርህ ጋር አጋባኝ በማለት አስቸገረችው፡፡ አባቷም ከሎሌው ጋር አጋባት፡፡

የለመኑትን የማይነሣ አምላክ ልብ ብላው የማታውቀውን የባለቤቷን ምሥጢር ገለጠላት፡፡ ቤተ ክርስቲያን እንደማይሔድ፣ እንደማያማትብ፣ ስመ እግዚአብሔርን እንደማይጠራ ልብ ብላ አስተውላው አታውቅም ነበር፡፡ ለምን እንደ ማያማትብ እና ወደ ቤተ ክርስቲያን እንደ ማይሔድ ስትጠይቀው ምሥጢሩን ሁሉ ነገራት፡፡ በሰማችው ነገር በጣም ደንግጣ ወደ ሊቀ ጳጳሱ ቅዱስ ባስልዮስ ሔዳ የገጠማትን ችግር ነገረችው፡፡ ቅዱስ ባስልዮስም ባልሽን ይዘሽው ነይ አላት፡፡ ሴቲቱም ባሏን ይዛ ወደ ቅዱስ ባስልዮስ ሔደች፡፡ ቅዱስ ባስልዮስም መዳን ይፈልግ እንደሆነ ጠየቀው፤ እሱም መዳን እንደ ሚሻ ለቅዱሱ ነገረው፡፡

እንዲነግረው ጠየቀው፡፡ የባለጸጋው አሽከርም ሰይጣናት ሲያስፈራሩት እንደ ሰነበቱ ነገረው፡፡ እሱም አበረታተቶ፣ ትንሽ እህል ካቀመሰው በኋላ ወደ ሱባኤው ቦታ መለሰው፡፡ እንደ ገና ከሦስት ቀን በኋላ አቅርቦ ጠየቀው፡፡ እሱም ድምፃቸውን እሰማለሁ እንጂ አላያቸውም ብሎ ነገረው፡፡ ባርባኛው ቀን ሲጠይቀው ሰይጣንን ጥለህ ስትቀጠቅጠው አየሁህ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ቅዱስ ባስልዮስ ካህናትን፣ መነኮሳትን እና ምእመናንን ሰብስቦ ምሕላ ያዘ፡፡ ኪርያላይሶን እያሉ በሚሰግዱበት ሰዓት ሰይጣን ቅዱስ ባስልዮስን አትጨቅጭቀኝ ብሎ ከአሽከሩ የወሰደውን ወረቀት በሕዝቡ ፊት ጣለለት፡፡ ቅዱሱም ፍጹም በእግዚአብሔር ላመነው አሽከር እና ለሚስቱ ሥጋውን እና ደሙን እንዳቀበላቸው መስከረም ፲፫ የሚነበበው ስንክሳር ያተርካል (ስንክሳር ከመስከርም እስከ የካቲት፣ ፲፱፻፹ ዓ.ም፥ ፳፩-፳፭)፡፡ በዚህ ዘመን ለችግር የተጋለጡትን የምንደግፈውም ከምግብና ልብስ ባለፈ እንዲህ ዘለዓለማዊ ሰላም እንዲያገኙ ጭምር መሆን አለበት፡፡✠